በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በስኳር ኮርፖሬሽን የመተሐራ ነባር ስኳር ፋብሪካ እና የኤታኖል ማስፋፊያ ሥራ አፈፃፀምና ውጤታማነት ላይ የተከናወነ

የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2009

አዲስ አበባ

ማውጫ

የኦዲት ግኝት ማጠቃለያ /Executive Summary/--I
ክፍል አንድ 1
መግቢያ.. 1
የስኳር ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ.. 1
የስኳር ኮርፖሬሽን ራዕይ እና ተልዕኮ.. 2
የስኳር ኮርፖሬሽኑ ዓላማዎች 2
የኮርፖሬሽኑ መብትና ግደታዎች 3
የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች 3
የሥራ ተቋራጮች ኃላፊነት 3
በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፍያ ሥራዎች.. 4
ከአማካሪ መሀንዲሶች የሚጠበቁ ተግባራት.. 4
የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል 4
የስኳር ኮርፖሬሽን የፋይናንስ ምንጭ 5
የኦዲቱ ዓላማ ፡-.. 5
የኦዲቱ አካባቢ.. 5
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች፡- 6
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት እና የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች፡-.. 6
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡-.. 7
ክፍል ሁለት 8
የኦዲቱ ግኝቶች.. 8
የኢታኖል ፕላንት ግንባታና ተከላ የጨረታ.. 8
ሂደትና ድርድር መደረጉን በተመለከተ.. 8
የስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ የኢታኖል ፕላንት በታቀደለት ጊዜና 9
በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ 9
የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት በማምረቻ ወጪና በጥራት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ.. 10
የስኳርና ተጓዳኝ ምርቶች እንዲመረቱ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ 10
ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት እና የማሽነሪ፣ 11
የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ 11
የስኳር ፋብሪካዎች የማምረት አቅም ፣ኢታኖል በተቀመጠ.. 17
እስታንዳርድ መመረቱን እና የፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ.. 17
የማሽነሪ እና የግብዓት አቅርቦት የሥራ መቆም.. 20
ችግርን ያቃለለ መሆኑን በተመለከተ.. 20

ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት ወጪ 24
ቆጣቢ በሆነ መልኩ መፈፀማቸውን በተመለከተ 24
የግዥ ፍላጎት በመርሀ-ግብር ተደግፎ 27
የሚፈፀም መሆኑን በተመለከተ 27
ኮርፖሬሽኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚፈፀም ግዥ በቂ 28
የስርጭት ሽፋን መጠቀሙን በተመለከተ 28
ቋሚ ንብረት ገቢ ከመደረጉ በፊት የንብረቱ ዓይነት 29
የተፈቀደው ስለመሆኑ መረጋገጡን በተመለከተ 29
ዓመታዊ የንብረት ቆጠራን /Inventory/ን በተመለከተ 31
ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ቋሚ ንብረቶች በንብረት አስተዳደር 34
መመሪያ መሰረት የተወገዱ መሆናቸውን በተመለከተ 34
ምርምርና ስልጠና የተሻሻለ የሸንኮራ አገዳ እና ስኳር አመራረት 36
ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ 36
ክፍል ሶስት 38
መደምደሚያ ሀሳቦች 38
ክፍል አራት 41
የማሻሻያሀሳቦች 41

የኦዲት ግኝት ማጠቃለያ/ Executive Summary/

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን እና በኢትዮጵያ የክዋኔኦዲት ደረጃዎች መሰረት በስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምና ውጤታማነት ላይ ከ 2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት ዓመት በተከናወኑ ተግባሮች የክዋኔ ኦዲት ያከናወነ ሲሆን የኦዲቱም ዓለማ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ላይ ያካሄዳቸውን የማስፋፍያ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን በተለይ ኦዲቱ በማስፋፍያ ዕቅድ የተያዙ የነባር ማስፋፍያ ሥራዎች፣የፋብሪካ ማስፋፍያ ግንባታ፣ተከላና የኮሚሽኒንግ ሥራዎች፣የመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ ማስፋፍያ ሥራዎችን አፈፃፀም እና ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፐሬሽን አፈፃፀም ውጤታመነትን በመገምገም በአሠራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ከነበሩ በመለየት ችግሮቹ የሚቀረፉበትን ወይም የሚሻሻሉበትን የማሻሻያ ሀሣቦች ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

ኦዲቱ በስኳር ኮርፖሬሽን እና በስሩ ባለ መተሐራ ስኳር ፋብሪካ የተከናወነ ሲሆን በኦዲቱ የተለዩት ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የኢታኖልፕላንቱ በ2008 በጀት ዓመት እስከ ግንቦት ወር ድረስ ከመተራ ስኳር ፋብሪካ ማግኘት በሚገባው የእንፋሎት ሃይል እጥረት ምክንያት ለ 111.67 ቀናት ምርት ሳያመርት የቆመ በመሆኑ፣ ከፕላንቱ ቡድን መሪ በተገኘ መረጃ መሰረት በቀን 40,000 ሊትር ሬክቲፋይድ ስፕሪት ጥቅል/የመጀመሪያ ደረጃ ምርት/ ቢመረትና ወደ ማምረት አቅም ቢቀየር በ 95% የጊዜ አጠቃቀም፡-= ብር 61,487,735 ማግኘት ይቻል እንደነበረ መታወቁ፣
- በ2008 በጀትዓመት በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የታንደም ቢ ወፍጮ ቁጥር 1 ተርባይን በእርጅና ምክንያት ከ 2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሥራ መሥመር በመውጣቱ ችግሩን ለመቅረፍ አዲስ የተርባይን ግዥ በ EI 13- 7630 ተጠይቆ የግዥ ሂደቱ በዩሮ 420,007.20 ተከናውኖ FIVES CAIL ካምፓኒ/የተርባይኑ ዙሪት/አዟዟር ከወፍጮ ዙሪት ጋር አንድ ሆኖ ባለመገኘቱ የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በሙሉ አቅሙ ባለመሥራቱ ለኢታኖል ፕላንቱ በበቂ ሁኔታ የእንፋሎት ሃይል መስጠት ያልቻለ መሆኑ መታወቁ፣
- በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ለኢታኖል ፕላንት/ፋብሪካ/ ግንባታና ተከላ የተመደበ መነሻ የኮንትራት ዋጋ ዩኤስ ዱ/USD/ 8,423,948.00 እና የኢትዮጵያ ብር 41,980,872.00 ሆኖ በድምር ብር 149,891,645.88 ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለፕሮጀክቱ የወጣው ወጪ 183,751,141.29 መሆኑ የተገለፀ ሆኖ፣ ይህም ብር 33,859,495.41/22.59%/ ከመነሻ ዋጋ ተጨማሪ የሚያሳይ ቢሆንም፣የተጨማሪ ክፍያን ምክንያት የሚያመለክት በአማካሪና በቀጣሪ

ድርጅት መካከል የተፈፀመ የውል ማስረጃ ያልቀረበ ከመሆኑም ባሻገር፤ ፕሮጀክቱ በታቀደለት ጊዜ መጠናቀቅን በተመለከተ እ.ኤ.አ 12/03/2009 ተጀምሮ እ.ኤ.አ 09/07/2011 በመጠናቀቁ የአራት ወራት መዘግየት የታየበት መሆኑ፣

- ኮርፖሬሽኑ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የኢታኖል ፕላት የተጠበቀውን ምርት ማምረት የሚያስችሉትን መለዋወጫዎች ማጥለያ/ዴካንተር/፣ የአልኮሆል እርሾ ለይቶ እንደገና ለመጠቀም የሚያገለግል መሳሪያ/ይስት ሰፐሬተር/፣ መበጥበጫ ማሽን/አጂቴተር ጊር ቦክስ/፣ ማጣሪያ ወንፊቶች/የሞሊክዩራ ሲቭ/ መለዋወጫዎችን ያላቀረበ በመሆኑ፤ በምርት ማምረት ሂደት ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፤እንዲሁም የኢታኖል ፕላንቱ ሥራውን የሚያከናውነው በመተሐራስኳር ፋብሪካ ላይ ጥገኛ በመሆን ከሚያገኘው የእንፋሎት ሃይል/እስቲም/በመሆኑ፤ስኳር ፋብሪካው የራሱ በሆኑ የመለዋወጫ ችግሮች በተደጋጋሚ ሲበላሽ ወይም ሲቆም የኢታኖል ፕላንቱም ለሥራው የሚያስፈልገውን የእንፋሎት ሃይል የሚያጣ በመሆኑ ለማሽነሪ ብልሽት/አልኮሆል ይዞ በመቆም መበላት ችግር/ እና ለምርታማነት ማነቆ ለሚሆኑ ቸግሮች ተጋላጭ መሆኑ፣
- የኢታኖል ፕላንት የምርት ሂደት በስኳር ፋብሪካው የእንፋሎት ሃይል አመንጪ ክፍል/ቦይለር/ በተደጋጋሚ መበላሸት ምክንያት ከ እ.ኤ.አ 10/04/16 ጀምሮ የኦዲቱ ቃለ-መጠይቅ መልስ እስከተሰጠበት 06/10/2008 ዓ.ም ማምረቱን ያቆመ መሆኑ፣
- የኢታኖልፕላንቱ በ 2008 በጀት ዓመት እስከ ግንቦት ወር ድረስ ለ 111.67 ቀናት ምርት ሳያመርት የቆመ በመሆኑ፤እነዚህ የተጠቀሱት ቀናት ከፕላንቱ ቡድን መሪ በተገኘ መረጃ መሰረት በቀን 40,000 ሊትር ረክቲፋይድ ስፒሪት ጥቅል/የመጀመሪያ ደረጃ ምርት/ ቢመረትና ወደ ማምረት አቅም ቢቀየር በ 95% የጊዜአጠቃቀም፡-

  =40,000x 111.67 x 0.95 = 4,243,460ሊትር ማምረት ይቻል የነበረ ሆኖ ወደ ገንዘብ ሲቀየር የ1 ሊትር ሬክቲፋይድ ስፒሪት/በመጀመሪያ ደረጃ በምርት ሂደት የሚመረት/

የመሸጫ ዋጋ ብር 14.49 በመሆኑ በዚህ ሂሳብ ሲሰላ፡- = 14.49x 4,243,460 = ብር 61,487,735 ማግኘት ይቻል እንደነበረ ሲገለፅ፤

ከኢታኖል የሥራ ክንውን ሪፖርት እ.ኤ.አ ነሀሴ 2015 /2007 ዓ.ም/ወራዊ ሪፖርት ከተወሰደ ዳታ አማካይ የቀን ጥቅል ረክቲፋይድ አልኮሆል ምርት 44,667 ሊትር በመሆኑ በዚህ መሰረት ለ 111.67 ቀናት የምርት ሂደት መቆም ቢሰላ፡-= 44,667x 111.67 x0.95 = 4,738,565.70 ሊትር ማምረትይቻል የነበረ ሆኖ ወደ ገንዘብ ቢለወጥ፡-

=14.49 x 4,738,565.70 = ብር 68,661,816.99 ማግኘት ይቻል የነበረ መሆኑ መታወቁ፣

- የታንደምቢ ወፍጮ ቁጥር 1 ተርባይን በእርጅና ምክንያት ከ 2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሥራ መሥመር በመውጣቱ ችግሩን ለመቅረፍ በማኔጅመንት ታምኖበት አዲስ የተርባይን ግዥበ EI 13- 7630 ተጠይቆ የግዥ ሂደቱ በዩሮ 420,007.20 ተከናውኖ FIVES CAIL ካምፓኒ/ የታንደም ቢ ወፍጮዎች ቲ-38 ተርባይን ብቸኛ አምራችና አቅራቢ/ ተከላውንም በሚያዚያ/2008 ያከናወነ ቢሆንም፤የተርባይኑ ዙሪት/አዟዟር ከወፍጮ ዙሪት ጋር አንድ ሆኖ አለመገኘቱ ሲሆን፤ ከላይ በተመለከቱት ችግሮች ምክንያት የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በመለዋወጫዎች እጥረት በሙሉ አቅሙ ባለመሥራቱ በፋብሪካው ላይ የሚፈጠር ችግር ለኢታኖል ፕላንቱ በበቂ ሁኔታ ለማምረት ሂደት የሚያገለግል የእንፋሎት ሃይል መስጠት ባለመቻሉ ከ2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት ዓመት የምርት ተፅኖ ማስከተሉ፣
- በግዥቁጥር MSD/1509 3700 Normal Overhaul /የሰራተኞች ዩኒፎርም/ እንዲገዛ ተጠይቆ በግልፅ ጨረታ በመውጣቱ በቀን 24/12/2005 የተከፈተ ሆኖ አስበሞ ኢንደስትሪል ኃ/የ/ግ/ማህበር ቫትን ጨምሮ በብር 705,266.25 ያቀረበ ቢሆንም በወቅቱ ግዥው ባለመከናወኑ በሌላ ጊዜ ከአዳማ ጋርመንት ቫትን ጨምሮ በብር 1,178,635.00 እንዲገዛ በመደረጉ ድርጅቱ በተመሳሳይ ግዥ ላይ ብር 437,368.75 ተጨማሪ ወጪ እንዲከፍል የተደረገ መሆኑ ማወቅ መቻሉ፣
- በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ አዲስ ተገዝቶ የተተከለ ቦይለር ፊድ ዋተር አናላይዘር/ለእንፋሎት ሃይል ማመንጨት የሚያስፈልገውን ውሃ የሚያጣራ/ ብር 1,906,362/ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ስድሳ ሁለት/ ለግዥ፣ለመጓጓዣና ለተለያየ ወጪ የተከፈለበት ከነባሩ ቴክኖሎጂ ጋር ባለመግጠሙ ምክንያት ከተተከለበት ቀን አንስቶ እስከ ኦዲቱ ወቅት ሰኔ/2008 ዓ.ም ከሁለት ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጥ የተቀመጠ መሆኑ፣
- ከውጭ ሀገር በመርከብ M.V Segalle D and M.V Serra ተጭኖ ከመጣ ስኳር ውስጥ በቁጥር 3,777/ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ሰባት/ ኩንታል ስኳር የተበላሸ በመሆኑ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ግቢ በመቅበር የድርጅቱ የማኔጅመንት አባላትን እና ሌሎች የመስተዳድር አካላትን በቁጥር 13 የሆኑ የስም ዝርዝራቸው የተመለከተ በወሰኑት ውሳኔ የተወገደ መሆኑን በሚያዚያ 13/2007 ዓ.ም ለማስወገድ በማኔጅመንት ከተያዘ ቃለ-ጉባኤ መመልከት የተቻለ ቢሆንም ስለሁኔታው በማስረጃ የተደገፈ መልስ ለመስጠት የቻለ አካል ያልተገኘ መሆኑ፣
- በምርምር የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች ገንዘብና ሀብት የወጣባቸው በመሆናቸው በስራ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከማድረግ አንፃር የተጠያቂነት ስርዓት በመዘርጋት ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ አለመሆኑ፣

ክፍል አንድ

መግቢያ

የስኳር ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ

1. ዘመናዊ የስኳር ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ በግል የውጭ ባለሀብቶችና በመንግስት ሽርክና በኩባንያ መልክ የተጀመረው በ 1946 ዓ.ም ከአዲስ አበባ 110 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው ወንጂ ከተማ ላይ ሲሆን፤ በወቅቱ በሽርክና ወደ ሥራ የገባው ኤች.ቪ.ኤ የተሰኘ የሆላንድ ኩባንያ ነበር፡፡ ኩባንያው 5 ሺህ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማልሚያ መሬት ተረክቦ ሰኔ 18 ቀን 1943 ዓ.ም ሥራ ጀመረ፡፡ የፋብሪካ ግንባታው መጋቢት 11 ቀን 1946 ዓ.ም ተጠናቀ ስኳር ማምረት ሲጀምር 1 ሺህ 400 ኩንታል ስኳር እያመረተምዕዙን/አንኳር/ እና ባለ አስር ሳንቲም እሽግ ስኳር ለገበያ ያቀርብ ነበር፡፡
2. በተመሳሳይም በኢትዮጵያ መንግስትና የሆላንድ ኩባንያ በሆነው ኤች.ቪ.ኤ መካከል በተደረሰው ስምምነት የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ሰኔ 26 ቀን 1957 ዓ.ም በአክስዮን መልክ ተመሰረተ፡፡ ከዓመታት በኋላ ፋብሪካው በ1962 ዓ.ም ከአዲስ አበባ 200 ኪሎሜትር ርቀት ላይ በምትገኘውና መርቲ ተብላ በምትታወቀው ቦታ ላይ ሥራ ጀመረ፡፡ በ 10ሺህ ሄክታር ላይ የሚለማ የሸንኮራ አገዳን በግብዓትነት የሚጠቀመው ይህ ፋብሪካ በአሁኑ ወቅት አማካይ ዓመታዊ የስኳር የማምረት አቅሙ 1 ሚሊዮን 300 ሺህ ኩንታል ሲሆን፤ እንዲሁም ኤታኖል 12.5 ሚሊዮን ሊትር ገደማ ነው፡፡
3. በ1967 ዓ.ም በተደረገው የመንግስት ለውጥ ምክንያት ስኳር ፋብሪካዎቹ በመንግስት ይዞታ ስር እንዲተዳደሩ ሆኑ፡፡ ይህን ተከትሎ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 58/1970 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን ወንጂ ሸዋና መተሐራ ስኳር ፋብሪካዎችን ጨምሮ አዲስ ከተማና አስመራ ከረሜላ ፋብሪካን እንዲያስተዳድር ተደረገ፡፡
4. የወንጂ ሸዋና የመተሐራ ስኳር ፋብሪካዎችን እንዲሁም የአዲስ ከተማንና የአስመራ ከተማን ከረሜላ ፋብሪካዎች ያስተዳድር የነበረው የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በ 1984 ዓ.ም በሕግ ሲፈርስ በምትኩ በደንብ ቁጥር 88/85 መተሐራ ስኳር ፋብሪካ፣ በደንብ ቁጥር 88/85 ወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እና በደንብ ቁጥር 199/86 ፊንጫአ ስኳር ፋብሪካ/በወቅቱ አዲስ የተጀመረ የስኳር ፕሮጀክት የነበረ/ እራሳቸውን የቻሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሆነው እንዲቋቋሙ ተደረገ፡፡

5. ይህ በእንዲህ እንዳለ ለስኳር ፋብሪካዎቹ የጋራ አገልግሎት እንዲሰጥ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል አክስዮን ማህበር በሶስቱ ስኳር ፋብሪካዎች፣ በልማት ባንክ እና በመድኅን ድርጅት በአክስዮን መልክ ህዳር 1990 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡

6. በኋላም የድጋፍ ሰጪ ማዕከሉን በማፍረስ የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 504/98 ተቋቁሞ የስኳር ፋብሪካዎቹን በመቆጣጠር፣ በፕሮጀክት ልማት፣በምርምር፣በስልጠናና በግብይት ረገድ ድጋፍ ሲሰጥ ቆየ፡፡ ይሁንና ከጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ኤጀንሲው እንዲፈርስ ተደርጎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003 የአሁኑ ስኳር ኮርፖሬሽን ተቋቋመ፡፡ ኮርፖሬሽኑ የስኳር ልማትን በአገራችን በስፋት ለማካሄድ በሚያስችለው መልኩ ተደራጅቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽን ራዕይ እና ተልዕኮ

ራዕይ

7. በቀጣይ እድገት ላይ በመመስረት በ2016 ዓ.ም በዓለም ተወዳዳሪ ከሆኑ 10 ግንባር ቀደም የስኳር ኢንዱስትሪዎች ተርታ መሰለፍ፤

ተልዕኮ

8. በአገሪቱ ያለውን እምቅ ሃብት ለማልማት የሚያስችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂና የሰው ሀይል አቅም በማፍራት ስኳር፤የስኳር ተረፈ ምርትና ተጓዳኝ ምርቶችን በማምረት የአገር ውስጥ ፍላጎትን ከማርካት ባሻገር የጎላ የኤክስፖርት ድርሻ በመያዝ የአገሪቱን እኮኖሚ መደገፍ፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽኑ ዓላማዎች

9. በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው

- የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ሌሎች ሰብሎችን ማልማት፤
- ስኳር፤ የስኳር ውጤቶችን፤ የስኳር ተረፈ ምርቶችን እና የስኳር ተረፈ ምርት ውጤቶችን በፋብሪካ ማዘጋጀትና ማምረት፤
- ምርቶቹንና ተረፈ ምርቶቹን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤
- አዳዲስና የማስፋፊያ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት፤ የዲዛይን ዝግጅት፤ የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፤የተከላ ኮሚሽኒንግ ሥራዎች እንድካሄዱ ማድረግ፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሸንኮራ አገዳና በስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ ጥናት ናምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ውጤቶችን በሥራ ላይ ማዋል፤

- አቅሙ ካላቸው የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና ፋብሬኬሽን ሥራዎች በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤
- በሕግ መሠረት ለሥራው የሚያስፈልገው መሬት ባለይዞታ መሆንና ማልማት፤
- የአገዳ ምርታቸውን ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያቀርቡ አገዳ አብቃዮችን ማበረታታትና መደገፍ፤
- ለስኳር ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፤መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትህምርት ተቋማት ጋር መተባበር፤
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጂ ሥራዎችን መሥራት ናቸው፡፡

የኮርፖሬሽኑ መብትና ግደታዎች

10. በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 88/1992 ተቋቁሞ የነበረው የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ፤ በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 89/1992 ተቋቁሞ የነበረው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ፤ በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 199/1994 ተቋቁሞ የነበረው የፊንጫአ ስኳር ፋብሪካ እና በአዋጅ ቁጥር 504/2006 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ መብትና ግደታዎች በደንብ ቁጥር 192/2006 ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች

የሥራ ተቋራጮች ኃላፊነት

11. ከተቋራጭ የሚጠበቁ ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-
    1. በገባው ውል መሰረት ዲዛይን መሥራት፣መፈብረክ በተጨማሪም ለግዥ የሚሆኑ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት፣ንዑስ ኮንትራት/ሰብ ኮንትራክት/ መስጠት፣ፋብሪካ ተከላ ማካሄድ እና ለፋብሪካው እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ ምቹ አቅርቦቶችን በጥንቃቄና በትጋት በውሉ መሰረት አሟልቶ መገኘት፣
    2. ተቋራጩ የኮንትራት ውል ሰጪው ድርጅት ያቀረበለትን ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳታዎችን /በመስክም በመገኘት ጭምር/በጨረታው አሸናፊነቱ በተሰጠው በ28 ቀናት ውስጥ በሚገባ መርምሮ ኮንትራት ውል ማፅደቅ አለበት፣
    3. ተቋራጩ ለሥራው የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች አሟልቶ ውል ከገባበት ቀን ጀምሮ ወደ ሥራ በመሰማራት ማጠናቀቅ በሚገባው ጊዜና የኮንትራት ዋጋ ማጠናቀቅ ናቸው፡፡

በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፍያ ሥራዎች

ከአማካሪ መሀንዲሶች የሚጠበቁ ተግባራት

12. ከአማካሪ መሀንዲስ የሚጠበቁ ሁለትኃላፊነቶች እንደምከተለው ቀርበዋል

1. አማካሪ ድርጅቱ ከተቋራጭ ጋር በሚያደርገው የየቀን ግንኙነት ሥራዎችን በእቅድ በመምራት ትክክለኛው ዲዛይን ሥራ ላይ መዋሉን ክትትል ማድረግ፣
2. ተቋራጭ የፋብሪካ ግንባታና ተከላን በሚገባ ማከናወኑን ግምገማ በማድረግ ማረጋገጥ፣
3. ሥራው በታቀደለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ በእቅድ መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ በየሳምንቱ በመደበኛ ፕሮግራም የፕሮጀክት ግምገማ ማከናወን ናቸው፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል

13. **የስኳር ኮርፖሬሽኑ አደረጃጀት**

ኮርፖሬሽኑ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን በስሩ የሚከተሉትን የሥራ ዘርፎች ይዞ ይገኛል፡፡ እነርሱም፡- የኮርፖሬት ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ኦዲት፣ኮርፖሬት ትራንስፎርሜሽንና ካይዘን ዘርፍ፣ኮርፖሬት መረጃና አይቲ ዘርፍ፣የአገዳ ተክል ልማትና ፋብሪካ ግንባታ ዘርፍ፣ ኦፕሬሽን ዘርፍ፣ኮርፖሬት እቅድና ፕሮጀክት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ፣ ኮርፖሬት የህዝብ ተሳትፎ ዘርፍ፣ ኮርፖሬት ፋይናንስ ዘርፍ፣ኮርፖሬት ሰው ሀብት አመራርና ልማት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ግብይት ዘርፍ፣ምርምርና ስልጠና ዘርፍ እና መስኖ፣ቤቶችና መሰረተ ልማት ዘርፍ ሆነው በስራቸው በአወቃቀር መግለጫው መረዳት እንደሚቻለው በዳይሬክቶሬቶች የተዋቀረ ነው፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽን የሰው ሃይል/2008 ዓ.ም/

ተ.ቁ	የፋብተሪካው /የፕሮጀክቱ ስም	በመዋቅርየተፈቀደየ ሰው ኃይል	በስራ ላይ ያለ የሰው ኃይል	ያልተሸፈኔ የስራ መደብ ብዛት	ከመዋቅር በላይ ያለ የሰው ኃይል	ምርመራ
1	ተንዳሆ	9,757	3,493	6,264		
2	ወንጂ/ሸዋ	2,605	3,726		1,121	
3	መተሐራ	2,514	3,203		689	
4	ፊንጫአ	3,205	3,270		65	
	አጠቃላይ	18081	13692	6264	1875	

ማስታወሻ፡- በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ቋሚ እና ኮንትራትን ጨምሮ ነው፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽን የፋይናንስ ምንጭ

14. ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር 41,999,731,264(አርባ አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ሳባት መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ አራት ብር) ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ብር 6,042,512,614(ስድስት ቢሊዮን አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ አስራ አራት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፌለዋል፡፡

ከ2006 እስከ 2008 በጀት ዓመታት ያለው የኮርፖሬሽኑ የበጀት አጠቃቀም የፋይናንስ ምንጭ በአባሪ ቁጥር ሁለት ተያይዟል፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽን የአሰራር ስርዓት መግለጫ/System Description/ በአባሪ ቁጥር ሶስት ተያይዟል፡፡

የኦዲቱ ዓላማ :-

15. የስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ላይ ያካሄዳቸውን የማስፋፍያ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን በተለይ ኦዲቱ በማስፋፍያ ዕቅድ የተያዙ የነባር ማስፋፍያ ሥራዎች፤የፋብሪካ ማስፋፍያ ግንባታ፤ተከላና የኮሚሽኒንግ ሥራዎች፤የመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ ማስፋፍያ ሥራዎችን አፈፃፀም እና ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፕሬሽን አፈፃፀም ውጤታመነትን በመገምገም በአሠራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ከነበሩ በመለየት ችግሮቹ የሚቀረፉበትን ወይም የሚሻሻሉበትን የማሻሻያ ሀሣቦች ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

የኦዲቱ አካባቢ

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ/Potential Audit area/ የስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ባካሄዳቸው የማስፋፍያ ሥራዎች በተለይ በእርሻና የፋብሪካ ማስፋፍያዎች አፈፃፀም፤ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፕሬሽን አፈፃፀም፤ለማስፋፍያ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አቅርቦት እንዲሁም ከማስፋፍያ ሥራዎች ጋር የተያያዙ የምርምርና ሥልጠና እና የአከባቢ ጥበቃ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለመከናወናቸው እና የማስፋፍያ ሥራዎችም ግልጽነት እና ተጠያቅነትን ባጠናከረ መልኩ የተካሄዱ ስለመሆናቸው ለመገምገም ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች፡-

17. ከላይ በተመረጠው የኦዲት አካባቢ /Potential Audit area/ሥር አራት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/ እና አምስት ንዑስ የትኩረት አቅጫዎች /Audit Sub Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የእርሻና የፋብሪካ ማስፋፊያዎች አፈፃፀምን መገምገም
   - 1.1 የፋብሪካ ግንባታና ተከላ አፈፃፀምን መገምገም
   - 1.2 የእርሻ ማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምን መገምገም
   - 1.3 ኮርፖሬሽኑ በሸንኮራ አገዳ ልማት የእርሻ መስፋፋት ምክንያት ለተነሱ/ ለሚነሱ የመሬት ባለይዞታዎች ካሳ ለሚገባቸው የካሳ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን መገምገም
2. የነባር ስኳር ፋብሪካዎች ከማስፋፊያ በኋላ ያለውን የኦፕሬሽን ሥራዎች አፈፃፀምን መገምገም
   - 2.1 የሸንኮራ አገዳ ልማት የእርሻ ኦፕሬሽን አፈፃፀምን መገምገም
   - 2.2 የፋብሪካ ኦፕሬሽን አፈፃፀምን መገምገም
3. ለፋብሪካ ማስፋፊያ ግንባታና ተከላ፣ ለመስኖ ግድብና ቦዮች እና የቤቶች ግንባታዎች የተገዙ ዕቃዎች/Materials/ የግዥ አፈፃፀም፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ የስኳር ኮርፖሬሽኑ ባዘጋጀው የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች መሰረት የተፈፀመ መሆኑን መገምገም
4. በስኳር /ኢታኖልፋብሪካዎች የሚገኙ የምርምርና ስልጠና ጣቢያዎች በምርምር ውጤታቸው የስኳር/ኢታኖል ምርትን ከመጨመር አንፃር ያስገኙትን ፋይዳ እና ከፋብሪካዎች ማስፋፋት ሥራ ጋር የአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤ እየተሰራ መሆኑን መገምገም የሚሉት ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት እና የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች፡-

18. እነዚህንም የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ንዑስ የኦዲት የትኩተረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 42 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative Criteria/ የተዘጋጁ ሲሆን፤በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የስኳር ኮርፖሬሽን ኃላፊዎች አስተያት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

- የስኳር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003
- የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የኮንትራት ውል ሰነድ 1 እና 2
- የስኳር ኮርፖሬሽን የአዲስ ሥራ ሂደት ቀረፃ/ቢፒ አር ሰነድ/ የካቲት 2004 ዓ.ም
- የስኳር ኮርፖሬሽን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሀምሌ 2003 ዓ.ም
- የስኳር ኮርፖሬሽን የንብረት አስተዳደር መመሪያ ጥቅምት 2005 ዓ.ም
- ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/1997

- የንብረት ካሳ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣ ደንብ 135/99
- የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች / ከ 2006- 2008 ዓ.ም የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ/
- የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች / ከ 2006- 2008 ዓ.ም የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ/
- አካባቢ ጥበቃን ከሚመለከት አዋጅ
- መልካም ተሞክሮዎችን በማካተት የተዘጋጀ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡-

የኦዲቱ ወሰን (Audit Scope)

19. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሻሻለው) በተሰጠው ሲልጣን መሠረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ 2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በስኳር ኮርፖሬሽን የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ የተሰራውን ሥራ ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በስኳር ኮርፖሬሽን ሲሆን፤ በስሩ ባለው መተሐራ ስኳር ፋብሪካ ነው፡፡

የኦዲቱ ዘዴ

20. በስኳር ኮርፖሬሽና የስኳር ፋብሪካው ግንባታ እና ተከላው በተከናወነበት መተሐራ ስኳር ፋብሪካ በመገኘት አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስ፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመገናኘት ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና የማስፋፊያ ሥራዎች አፈጻጸምን አስመልክቶ በአካል በመገኘት መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን የክዋኔ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች

የኢታኖል ፕላንት ግንባታና ተከላ የጨረታ

ሂደትና ድርድር መደረጉን በተመለከተ

21. ለነባር ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ግንባታና ተከላ የጨረታ ሂደትና ድርድር ሊከናውን ይገባል፡፡
22. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ግንባታና ተከላ የጨረታ ሂደትና ድርድር ያከናወነ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ለኢታኖል ፕላንት ግንባታና ተከላ ሁለት ካምፓኒዎች አንግሊክ ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ካምፓኒ እና ኬቢኬ ኬም ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ካምፓኒ ብቻ የጨረታ ሂደትና ድርድር የተካሄደ መሆኑ ከኢታኖል ተርን ኪ ፕሮጀክት /ሥራን አጠናቆ ፋብሪካን አስነስቶ ማስረከብ/ ከሚል ቴክኒካዊ ግምገማ እ.ኤ.አ ጥር/2009 ሰነድ መረዳት የተቻለ በመሆኑ፤በወቅቱ የነበረው የጨረታ ኮሚቴ ሁለቱን ብቻ ለማወዳደር ከውሳኔ የደረሰበትን ምክንያት የሚያሳይ ቃለ-ጉባኤ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካም ሆነ በስኳር ኮርፖሬሽን ያልተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡
23. ስለ ሁኔታው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የግዥ ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የኢታኖል ፕላንት ተርን ኪ ፕሮጀክት መነሻ እ.ኤ.አ ከ 2008 ጀምሮ በመሆኑ እና ከስምንት ዓመታት በላይ በማስቆጠሩ በግዥ ቡድን በኩል የተሟላ መረጃ ተጠቃሎ ማግኘት ያዳገተ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
24. የጨረታ ሂደት እና ድርድር የተከናወነባቸውን ማስረጃዎችን በተደራጀ ሁኔታ ይዞ በሚፈለጉበት ወቅት ማቅረብ አለመቻል የተሰራውን ሥራ ተዓማኒነት የሚያሳጣው ከመሆኑም በላይ ለብልሹ አሰራር መንስኤ ይሆናል፡፡

የስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ የኢታኖል ፕላንት በታቀደለት ጊዜና

በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ

25. ኮርፖሬሽኑ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓትን ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የፋብሪካ ግንባታና ተከላ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ እስከ ኮሚሽኒንግ ሥራ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡

26. ኮርፖሬሽኑ ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት የፋብሪካ ግንባታ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ እስከ ኮሚሽኒንግ ሥራ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ተረፈምርትን/ሞላሰስ/ ጥቅምላይ ለማዋል ለኢታኖል ፕላንት/ፋብሪካ/ ግንባታና ተከላ የተመደበ መነሻ የኮንትራት ዋጋ ዩኤስ ዲ/USD/ 8,423,948.00 እና የኢትዮጵያ ብር 41,980,872.00 ሆኖ በድምር ብር 149,891,645.88 ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለፕሮጀክቱ የወጣው ወጪ 183,751,141.29 መሆኑ የተገለፀ ሆኖ፣ ይህም ብር 33,859,495.41/22.59%/ ከመነሻ ዋጋ ተጨማሪ የሚያሳይ ቢሆንም፣የተጨማሪ ክፍያን ምክንያት የሚያመለክት በአማካሪና በቀጣሪ ድርጅት መካከል የተፈፀመ የውል ማስረጃ ያልቀረበ ከመሆኑም ባሻገር፣ ፕሮጀክቱ በታቀደለት ጊዜ መጠናቀቅን በተመለከተ እ.ኤ.አ 12/03/2009 ተጀምሮ እ.ኤ.አ 09/07/2011 በመጠናቀቁ የአራት ወራት መዘግየት የታየበት መሆኑ ታውቋል፡፡

27. ስለ ሁኔታው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የፋይናንስ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከላይ የቀረቡትን የኮንትራት ውል መነሻ ዋጋ እና ሥራው የተጀመረበትን እና የተጠናቀቀበትን ብቻ ሆኖ ዋጋ ጭማሪና የጊዜ መራዘምን በተመለከተ መልስ ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

28. በኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታ ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ማስተባበር፣ መቆጣጠርና ማረጋገጥ ከመሆኑ አንፃር ያልተገበረ በመሆኑ ሀገሪቷ ለሌላ ልማት ልታውለው የምትችለው ሀብት ለተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ እንዲውል አድርጓል፡፡

የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት በማምረቻ ወጪና በጥራት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ

የስኳርና ተጓዳኝ ምርቶች እንዲመረቱ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ

29. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ኢታኖል ፕላንት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣ ክትትል ማድረግና መቆጣጠር/ በማምረቻ ወጪና በጥራት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የስኳር ምርትና ተጓዳኝ ምርቶች እንዲመርቱ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

30. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ኢታኖል ፕላንት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠቱን፣የክትትልና ቁጥጥር ሥራ መሥራቱን፤እንዲሁም በማምረቻ ወጪና በጥራት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የስኳር ምርትና ተጓዳኝ ኢታኖል ምርት እንዲመረቱ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፤ ኮርፖሬሽኑ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የሞላስስ ተረፈ ምርትን ጥቅም ላይ ለማዋል ኢታኖል አልኮሆል ማምረት የሚችል ኢታኖል ፕላንት ግንባታና ተከላ ያካሄደ ቢሆንም፤ፕላንቱ የተጠበቀውን ምርት ማምረት የሚያስችሉትን መለዋወጫዎች ማጥለያ/ዴካንተር/፣ የአልኮሆል እርሾ ለይቶ እንደገና ለመጠቀም የሚያገለግል መሳሪያ/ይስት ሰፐሬተር/፣ መበጥበጫ ማሽን/አጂቴተር ጊር ቦክስ/፣ ማጣሪያ ወንፊቶች/የሞሊክዩራ ሲቭ/ መለዋወጫዎችን ያላቀረበ በመሆኑ፤ በምርት ማምረት ሂደት ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፤እንዲሁም የኢታኖል ፕላንቱ ሥራውን የሚያከናውነው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ላይ ጥገኛ በመሆን ከሚያገኘው የእንፋሎት ሃይል/እስቲም/በመሆኑ፤ስኳር ፋብሪካው የራሱ በሆኑ የመለዋወጫ ችግሮች በተደጋጋሚ ሲበላሽ ወይም ሲቆም የኢታኖል ፕላንቱም ለሥራው የሚያስፈልገውን የእንፋሎት ሃይል የሚያጣ በመሆኑ ለማሽነሪ ብልሽት/አልኮሆል ይዞበመቆም መበላት ችግር/ እና ለምርታማነት ማነቆ ለሚሆኑ ቸግሮች ተጋላጭ መሆኑ ታውቋል፡፡

31. ስለ ሁኔታው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ለኢታኖል ምርት ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በአቅም ውስንነት ምክንያት ችግር የፈጠሩ ማሽነሪዎች ዴካንተር፣ ይስት ሰፓሬተር፣ ፌርመንተር ቁጥር 4 አጊቴተር ጊር ቦክስ እና የሞላስስ ሚዛን በብር እጥረት ምክንያት ያልተገዙ መሆናቸውን ገልፀው ለኢታኖል ፕላንቱ ማምረት የእንፋሎት ሃይል የሚገኘው ከመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በመሆኑ ፋብሪካው የመለዋወጫ ችግር ሲያጋጥመው በቂ የእንፋሎት ሃይል ማመንጨት የማይችል በመሆኑ የኢታኖል ፕላንቱም ጥገኛ በመሆኑ ሥራውን ማቆም የሚገደድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

32. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታ ኦፕሬሽን ከተሰጠው ተግባር የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ በጥራት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የስኳር ምርትና ተጓዳኝ ምርቶች ማምረት እና ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊትር ኢታኖል እንዲመረት ማድረግ ከሚለው አኳያ ለስኳር ፋብሪካውና ለኢታኖል ፕላንቱ የመለዋወጫ ድጋፍ ባለመደረጉ በእንፋሎት ሃይል እጥረት ምክንያት የሚቆም በመሆኑ ኢታኖል ፕላንቱ ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊትር ኢታኖል የማምረት አቅሙን እንዳይወጣ ሆኖ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፆ እንዲታጣ አድርጓል፡፡

ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት እና የማሽነሪ፣

የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ

33. ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር፣እንዲሁም የማሽነሪ፣ የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ /ሀብትን አዛውሮ በመጠቀም/ ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ ግብዓቶችን በወቅቱ እንዲቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡

34. ኮርፖሬሽኑ በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገና እና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር ድጋፍ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፤ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የሞላስስ ተረፈ ምርትንጥቅምላይበማዋልኢታኖል አልኮሆል/ከሞላስስ በሁለተኛ ደረጃ የማምረት ሂደት የሚመረት/ በማምረት በነዳጅ ከ 5- 10 ፐርሰንት የሚቀላቀል እና ረክቲፋይድ ስፕሪት / በማምረት ሂደት በአንደኛ ደረጃ የሚመረት/ ለተለያዩ የመጠጥ ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት ሽያጭ የሚውል በማምረት ላይ የሚገኘው የኢታኖል ፕላንት የምርት ወቅት/Production campaign period/ እንጂ፤ ከስኳር ፋብሪካው ተነጥሎ የራሱ ዘመናዊ የጥገና አገልግሎት የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

35. በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማሽነሪ፣ የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ የሰጠ ስለመሆኑ፣ ሀብትን አዛውሮ ጥቅም ላይ በማዋል ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ ግብዓቶችን በወቅቱ እንዲቀርቡ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ❖ የመተሐራ ኢታኖልፕላንት በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ላይ በጥገኝነት ሙሉ ለሙሉ የተመሰረተ በመሆኑ ፋብሪካው ችግር ሲገጥመው ኢታኖል ፕላንቱ በእንፋሎት እጥረት ሥራ የሚያቆም መሆኑ ታውቋል፡፡
- ✓ የኢታኖል ፕላንት የምርት ሂደት በተለያየ ጊዜ በመብራት መቆራረጥና በእንፋሎት ሃይል እጥረት እየቆየ ቢነሳም፤ በስኳር ፋብሪካው የእንፋሎት ሃይል አመንጪ ክፍል/ቦይለር/ በተደጋጋሚ መበላሸት ምክንያት ከ እ.ኤ.አ 10/04/16 ጀምሮ የኦዲቱ ቃለ-መጠይቅ መልስ እስከተሰጠበት 06/10/2008 ዓ.ም ማምረቱን ያቆመ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ✓ የኢታኖል ፕላንቱ በ 2008 በጀት ዓመት እስከ ግንቦት ወር ድረስ ለ 111.67 ቀናት ምርት ሳያመርት የቆመ በመሆኑ፤ እነዚህ የተጠቀሱት ቀናት ከፕላንቱ ቡድን መሪ በተገኘ መረጃ መሰረት በቀን 40,000 ሊትር ሬክቲፋይድ ስፒሪት ጥቅል/የመጀመሪያ ደረጃ ምርት/ ቢመረትና ወደ ማምረት አቅም ቢቀየር በ 95% የጊዜ አጠቃቀም፡-

= 40,000x 111.67 x 0.95 = 4,243,460ሊትር ማምረት ይቻል የነበረ ሆኖ ወደ ገንዘብ ሲቀየር የ 1 ሊትር ሬክቲፋይድ ስፕሪት/በመጀመሪያ ደረጃ በምርት ሂደት የሚመረት/ የመሸጫ ዋጋ ብር 14.49 በመሆኑ በዚህ ሂሳብ ሲሰላ፡-

- = 14.49x 4,243,460 = ብር <u>61,487,735</u> ማግኘት ይቻል እንደነበረ ሲገለፅ፤ ከኢታኖል የሥራ ክንውን ሪፖርት እ.ኤ.አ ነሀሴ 2015 /2007 ዓ.ም/

ወራዊ ሪፖርት ከተወሰደ ዳታ አማካይ የቀን ጥቅል ረክቲፋይድ አልኮሆል ምርት 44,667 ሊትር በመሆኑ በዚህ መሰረት ለ 111.67 ቀናት የምርት ሂደት መቆም ቢሰላ፡-

= 44,667x 111.67 x0.95 = 4,738,565.70 ሊትር ማምረትይቻል የነበረ ሆኖ ወደ ገንዘብ ቢለወጥ፡-= 14.49 x 4,738,565.70 = ብር <u>68,661,816.99</u> ማግኘት ይቻል የነበረ መሆኑ ታውቋል፡፡

36. ለኢታኖል ፕላንት ማምረት ሂደት ዋና መንስኤዎች የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የተለያዩ ወሳኝ መለዋወጫዎችን በወቅቱ ባለማግኘቱ ከአቅም በታች በመሥራቱ ለፕላንቱ የማምረት ሂደት በብቃት የእንፋሎት ሃይል መስጠት አለመቻሉ መሆኑ ታውቋል፡፡
37. የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ለምርት ግብዓት የሆኑ መለዋወጫዎችን በወቅቱ አለማግኘቱን በተመለከተ ከ 2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን ፋብሪካው ያጋጠሙት ችግሮች በየበጀት ዓመቱ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተመልክቷል፡-
   - ✓ በ 2006 በጀት ዓመት ለስኳር ፋብሪካው ከአቅም በታች መሥራት ዋና ምክንያቶች የሆኑ፡-
   - የሚል ተርባይን ቦክስ መሰበር/የወፍጮ ማንቀሳቀስን የሚሰራ/፤
   - የቦይለር ቁጥር 4/ የእንፋሎት ሃይል ማመንጫ / የሥራ ክንውን አቅሙ አጥጋቢ ባለመሆኑ ምክንያት በፕሮጀክትነት ይዞ ሲሰራ የነበረው ካምፓኒ በኮንትራት ስምምነቱ መሰረት ሥራውን ያለማጠናቀቅ ችግር፣
   - የታንደም ቢ ወፍጮ/ የሸንኮራ አገዳ መፍጪያ/በተለየዩ ምክንያቶች ከሥራ መስመሩ እንዲወጣ መደረግ፤በአጠቃላይ ለስኳር ፋብሪካው የእንፋሎት ሃይል እና ሃይል የማመንጨት/Power Generation/ ችግሮች መሆናቸው ታውቋል፡፡

38. በ2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን ስኳር ፋብሪካው የቦይለር ፕላንት/የእንፋሎት ሃይል ማመንጫው/ የሥራ ክንውን አቅሙ ያነሰ መሆኑና የዲፊውዘር ፕላንቱ/አገዳ መጭመቂያ ክፍል/ በተደጋጋሚ መበላሸት ዋና ምክንያቶች ሲሆኑ፤ እነርሱም፡-

- የታንደም ቢ/የሸንኮራ አገዳ መፍጪያ/ የመጀመሪያው ወፍጮ ጊር ቦክስ/ሃይልን ለመጨመር ወይም ለመቀነስ የሚያስችል/ የጥርስ መሸራረፍ የተነሳ በመበላሸት፣
- ዲፊውዘር ፓወር ተርባይን 3 ቁጥር በብልሽት ምክንያት ከሥራ መስመሩ በመውጣቱ የተነሳ የሃይል መጠን/ሎድ/ መቀነስ፣
- የአሮጌውና የአዲሱ ወፍጮ ፋይብራይዘር ቆንጨራ/አገዳ ወደ ወፍጮ ክፍል ከመግባቱ በፊት የሚሰነጣጥቅ/ በመደነዙ ምክንያት በተደጋጋሚ ግደባ/እገዳ /ብሎኬጅ/ በማስከተሉ፤እንዲሁም ቦይለር /የእንፋሎት ሃይል ማመንጫ/ ቁጥር 2 ቱቦ በመቀደዱ ቦይለሩ ለጥገና ከሥራ መስመሩ መውጣት፣

የዲፊውዘር ፕላንት ታንደም ኤ መቆም፡-

- ኤቫፖሬሽንና ቫኪዩም ፕላንት በእንፋሎት ሃይል እጥረት እና በኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥ ምክንያት በተደጋጋሚ ከሥራ መስመራቸው ውጪ የመሆን ችግር የሚያጋጥም መሆኑ፣
- በስኳር ፋብሪካው አዲስ የተተከለው ቦይለር ፊድ ዋተር/TOC/ አናላይዘር ብር 1,906,362/አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ስድሳ ሁለት/ ወጪ የወጣበት ከህንድ አገር ተገዝቶ የመጣ ከነባሩ ቴክኖሎጂ ጋር ባለመግጠሙ ምክንያት ከተተከለበት ቀን አንስቶ ከሁለት ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጥ የተቀመጠ መኖሩ፣

39. በ2008 በጀት ዓመት የታንደም ቢ ወፍጮ ቁጥር 1 ተርባይን በእርጅና ምክንያት ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሥራ መሥመር በመውጣቱ ችግሩን ለመቅረፍ በማኔጅመንት ታምኖበት አዲስ የተርባይን ግዥ በ EI 13- 7630 ተጠይቆ የግዥሂደቱ በዩሮ 420,007.20 ተከናውኖ FIVES CAIL ካምፓኒ/ የታንደም ቢ ወፍጮዎች ቲ-38 ተርባይን ብቸኛ አምራችና አቅራቢ/ ተከላውንም በሚያዚያ/2008 ያከናወነ ቢሆንም፤የተርባይኑ ዙሪት/አዚዚር ከወፍጮ ዙሪት ጋር አንድ ሆኖ አለመገኘቱ ሲሆን፤ ከላይ በተመለከቱት ችግሮች ምክንያት የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በመለዋወጫዎች እጥረት በሙሉ አቅሙ ባለመሥራቱ በፋብሪካው ላይ የሚፈጠር ችግር ለኢታኖል ፕላንቱ በበቂ ሁኔታ ለማምረት ሂደት የሚያገለግል የእንፋሎት ሃይል መስጠት

ባለመቻሉ ከ2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት ዓመት በሚከተለው ቅደም ተከተል መሰረት የምርት ተፅኖ ተከስቷል፡፡

- በ 2006 በጀት ዓመት 3,078.3 ኪሎ ሊትር ረክቲፋይድ ስፕሪት/ የመጀመሪ ደረጃ ምርት/ ለማምረት ታቅዶ 4,677.61 ሊትር የተመረተ ሲሆን፤ ይህም እቅዱን 1,599.31 በመብለጥ የተመረተ መሆኑ/ በመብለጥ የተመረተበት ምክንያት የፕላንቱ ዋና ዓላማ ኢታኖል አልኮሆል/ፓወር አልኮሆል/ማምረት በመሆኑ ይህም አልኮሆል የእንፋሎት ሃይል በበቂ አቅም በሚኖርበት ጊዜ የሚመረት የፕላንቱ ሁለተኛ ደረጃ ምርት በመሆኑ ሆኖ፤ሆኖም ግን የእንፋሎት ሃይል በበቂ አቅም
  የማይገኝ ሲሆን ፕላንቱ የመጀመሪያ ደረጃ ምርቱን ረክቲፋይድ ስፕሪት አልኮሆል እንዲያመርት የሚገደድ በመሆኑ ከታቀደው እቅድ በላይ የተመረተ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ኢታኖል/ፓወር አልኮሆል 7,182.70 ኪሎ ሊትር ለማምረት ታቅዶ 3,864.79 ኪሎ ሊትር የተመረተ ሲሆን፤ ይህም 3,317.91 ኪሎ ሊትር ያነሰ መሆኑ፣

ለታንዳም ቢ ወፍጮ ቁጥር 1 የተገዛ አዲስ ተርባይን በእስፐስፊከሽን ችግር ምክንያት ከዎፍጮ ዙሪት ጋር ተጣጥሞ ባለመገኘቱ ሥራ ላይ ሳይ ውል የቀረን የሚያሳይ ፎቶግርፍ

40. በ 2007 በጀት ዓመት ለማምረት ታቅዶ ከነበረ 3,700 ኪሎ ሊትር ረክቲፋይድ ስፕሪት 3,298.3 የተመረተ ሲሆን፤ ይህም 401 ኪሎ ሊትር ያነሰ ሲሆን፤ እንዲሁም ኢታኖል/ፓወር/አልኮሆል 7,300ኪሎ ሊትር ለማምረት ታቅዶ 5,508 ኪሎ ሊትር የተመረተ በመሆኑ 1,792 ኪሎ ሊትር ያነሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

41. በ 2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 1,697.7 ኪሎ ሊትር ረክቲፋይድ ስፕሪት ለማምረት ታቅዶ 3,833.8 ኪሎ ሊትር የተመረተ በመሆኑ፤ ይህም 2,136.1 ኪሎ ሊትር መብለጥ የሚያሳይ መሆኑ/ የተሰጠው ምክንያት በበቂ ሁኔታ የእንፋሎት ሃይል በማይኖርበት ጊዜ የመጀመሪ ደረጃ ምርትን ለማምረት አስገዳጅ ሁኔታ የሚፈጠርመሆኑ/፤ስለሆነም በዚህ ወቅት የፕላንቱ ዋና ዓለማ የሆነው የኢታኖል/ፓወር/ አልኮሆል 5,600 ኪሎ ሊትር ለማምረት ታቅዶ 690.68 ኪሎ ሊትር የተመረተ በመሆኑ 4,909.32 ኪሎ ሊትር ያነሰ መሆኑ፤ ከላይ የተመለከተው የ 2008 በጀት ዓመት ምርት እስከ ሚያዚያ መጨረሻ ያለውን ብቻ ያካተተ ሲሆን፤ የኢታኖል ፕላንቱ በግንቦት ወር በእንፋሎት ሃይል እጥረት ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ማምረት ያቆመ መሆኑ ታውቋል፡፡

በኦዲቱወቅትየማምረትሥራውንአቁሞየታየውየኤታኖልፕላንት/በነባራዊ ሁኔታ በተሰጠ አስተያትም እስከ 04/01/2017 ኢታኖል/ፓወር አልኮሆል ማምረቱን እንዳልጀመረ ታውቋል/

42. በተጨማሪም በኦዲቱ ኢ.ታኖል ፕላንቱ ማምረቱን አቁሞ በአካል በታየበት ወቅት በኢ.ታኖል በልክ ታንከር/ ግዙፍ የሞላስስ ማከማቻ ጎተራ/ 10,000,000 ሊ.ትር/14,100 ቶን/ ሞላስስ የሚገኝ መሆኑ ሲገለፅ፤ በፕላንቱ መስመር ላይ ያለ/በምርት ሂደት ላይ ያለ/ ወደ ምርት ያልተቀየረ/ያልተለወጠ 450,000 ሊ.ትር/634.5 ቶን/ ሞላስስ ያለ በመሆኑ፤ ሞላስስ ከ 6 ወራት በኋላ የስኳር ይዘቱ በሂደት የሚቀንስ በመሆኑ፤ለረጅም ጊዜ ከቆየ የስኳር ይዘቱ ከ 40% በታች ስለሚሆን ለፕላንቱ ምርት ግብዓትነት የማያገለግል መሆኑ ታውቋል፡፡

43. ለማሳያ በታንከር ውስጥ ያለው ሞላስስ ወደ ኢ.ታኖል አልኮሆል ቢቀየር

ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊ.ትር የሚመረት መሆኑ በእስታንዳርድ በተቀመጠው መሰረት፡-

14,100 x 280= 3,948,000 ሊ.ትር ኢ.ታኖል አልኮሆል

ወደ ብር ሲለወጥ 1 ሊ.ትር ኢ.ታኖል 9.50 ሆኖ ቢሰላ

3,948,000x 9.50= ብር 37,506,000

- በሥራ ሂደት ላይ ያለ ወደ ምርት ያልተቀየረ 450,000 ሊ.ትር/634.5 ቶን/

634.5 x 280 = 177,660 ሊ.ትር ኢ.ታኖል አልኮሆል ወደ ብር ሲለወጥ

177,660 x 9.50 = ብር 1,687,770

በድምሩ በምርት ሂደት ላይ ያለና በታንከር ውስት ያለ ሞላስ ወደ ኢ.ታኖል አልኮሆል ቢለወጥ ፡-

ብር 37,506,000 + ብር 1,687,770 = ብር 39,193,770 ማግኘት ይቻል እንደነበር ታውቋል፡፡

44. ስለሁኔታው የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅና የኢ.ታኖል ፕላንት ምርት ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የፋብሪካ አጠቃላይ የእንፋሎት ሃይል ማመንጨት ችግርን ለመፍታት ጥናት እንዲደረግ ተፈቅዶ አጥኚ ለመቅጠር ቢ.ጋር/ TOR/ ተዘጋጅቶ ጨረታ ወጥቶ ጥናቱን ለማድረግ ሶስት አቅራቢዎች የቀረቡ ሆነው የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ የፋይናንሻል ግምገማ እየተጠበቀ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፤ የኢ.ታኖል ፕላንቱ የምርት ቡድን መሪ የኢ.ታኖል ፕላንቱ የስኳር ፋብሪካው ጥገኛ በመሆኑ የፋብሪካው እንፋሎት አመንጪ ክፍል ቦይለር ተደጋጋሚ ብልሽት ሲደርስበት በእንፋሎት ሃይል እጥረት የኢ.ታኖል የማያመርት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

45. የስኳር ኮርፖሬሽኑ ከተሰጠው ቁልፍ ተግባር በቂ የቴክኒካል ድጋፍን ክትትል በማድረግ በመስጠት የፋብሪካዎችን ምርታማነት ማሳደግ፣የወጪ ቅነሳ እስትራተጂ እንዲተገብሩ መደገፍ፣ መከታተልና መቆጣጠር የሚል ቢሆንም የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በምርት ሂደቱ የሚያስፈልጉት መለዋወጫዎች በተፈለገው ሁኔታ ባለማግኘቱ ከ 2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን የመለዋወጫ ችግሮች የገጠሙት በመሆኑ ለኢታኖል ፕላንቱ/ፋብሪካ/ ማምረት ሂደት የሚያስፈልግ የእንፋሎት ሃይል ማቅረብ ባለመቻሉ ከምርት ሊያገኝ የሚችለውን ብር 68,661,816.99 እንዲያጣ የተደረገ ሲሆን፣ በግብዓትነት ሊውል የሚችል ሞላስስም ብር 39,193,770 እንዲባክን ሆኗል፡፡

የስኳር ፋብሪካዎች የማምረት አቅም ፣ኢታኖል በተቀመጠ

እስታንዳርድ መመረቱን እና የፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ

46. የስኳር ፋብሪካዎች ስኳር የማምረት አቅም /Over all Recovery/ 86-88%መድረሱን፣እንዲሁም ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊትር ኢታኖል መመረቱ ክትትል ሊደረግ እና ዘመናዊ የማሽነሪ ጥገናና እድሳት ስርዓት በመዘርጋት አጠቃላይ የፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀም 90% የደረሰ መሆኑን በማረጋገጥ ከ 87% በታች እንዳይወርድ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

47. ኮርፖሬሽኑ የነባር ስኳር ፋብሪካዎች ስኳር የማምረት አቅም/Over all recovery/ 86- 88% መድረሱን፣ እንዲሁም ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊትር ኢታኖል መመረቱን የተከታተለና የደገፈ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣ የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ለገጠመው የመለዋወጫ እጥረት ድጋፍ ባለማድረጉ ፋብሪካው በ 2006 በጀት ዓመት የፋብሪካ የማምረት አቅም የዓመቱ እቅድ 88% ሆኖ አፈፃፀሙ 81.9% መሆኑ ሲታወቅ፣ በ 2007 በጀት ዓመት የፋብሪካ የማምረት አቅም የዓመቱ እቅድ 88% ሆኖ አፈፃፀሙ 83.54% ሲሆን፣ በ 2008 በጀት ዓመት የዓመቱ እቅድ 84.17% ሆኖ አፈፃፀሙ 76.98% መሆኑ ታውቋል፡፡

48. ሞላስስን በተመለከተ በ 2006 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 43,144.1 ቶን ሞላስስ ለኢታኖል ምርት ጥቅም ላይ በማዋል 7,182.70 ኪሎ ሊትር ኢታኖል/ፓወር/ አልኮሆል ለማምረት ታቅዶ ሊመረት የቻለው 36,038 ቶን ሞላስስን ሥራ ላይ በማዋል፣ /በማነስ 7,106ቶን ሞላስስ/ 3,864.79/53.81%/ ኪሎ ሊትር ኢታኖል አልኮሆል በ 3,317.91/46.19% ኪሎ ሊትር በማነስ መመረቱ ታውቋል፡፡ ይህም እቅዱን መሰረት አድርጎ ሲሰላ ከ 1 ቶን 166.48 ሊትር ለማምረት ታቅዶ ከ 1 ቶን 107.24 ሊትር መመረቱን የሚሳይ በመሆኑ በኮርፖሬሽኑ በተቀመጠው እስታንዳርድ ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊትር መመረት አለበት ከሚላው ያነሰ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑ ታውቋል፡፡

49. በ 2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 38,001.1 ቶን ሞላሰስ ጥቅም ላይ በማዋል 7,300 ኪሎ ሊትር ኢታኖል ለማምረት ታቅዶ ተግባራዊ ሊሆን የቻለው 35,209 ቶን ሞላሰስ /በማነስ 2,792 ቶን/ ጥቅም ላይ በማዋል 5,508.0/75.45%/ ኪሎ ሊትር /በ 1,792/24.55%/ ኪሎ ሊትር በማነስ/ መመረቱ ታውቋል፡፡

50. በ 2007 በጀት ዓመት የመተሐራ ኢታኖል ፕላንት በኤሌክትሪክ መቆራረጥ 148 ሰዓት እና በፕላንቱ የሥራ እንቅስቃሴ ወቅት በማሽኖች ላይ በሚታይ ግግር/እስኬል/ 178.8 ሰዓት በድምሩ 326.8 ሰዓት በቀናት ሲቆጠር 13.61 ቀናት በመቆሙ ማምረት አለመቻሉ የታወቀ ሲሆን፣ፕላንቱ ማምረት ባልቻለባቸው ቀናት ውስጥ በጥቅል አመራረት/አንደኛ ደረጃ ምርት ረክቲፋይድ ስፒሪት አልኮሆል/ ለ 13.6 ቀናት እና በተናጠል እቅድ መሰረት 70 ከመቶ ኢታኖል እና 30 ከመቶ ረክቲፋይድ ስፒሪት ቢመረት የሚመጣው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

- ጥቅል ምርት = 13.6 x 43,292/ጥቅል የቀን የማምረት አቅም ከ 2007 በጀት ዓመት ሪፖርት/= 588,771.2 ሊትር አልኮሆል ሲሆን፣
- በተናጠል ኢታኖል/ፓወር/ አልኮሆል = 0.7 x 588,771.2= 412,139.8 ሊትር ማምረት ይቻል የነበረ መሆኑ፣

  በገንዘብ ሲሳላ 412,139.8 ሊትር x 9.50 = ብር 3,915,328.10 ሲሆን፣
- ረክቲፋይድ ስፒሪት= 0.3 x 588,771.2= 176,631.4 ሊትር

  በገንዘብ ሲሰላ 176,631.4 x 14.49 = ብር 2,559,388.99

  በድምሩ ፡- ብር6,474,717.09

የነበረ መሆኑ ታውቋል፡፡/የኢታኖል ፕላንቱ የቀን ምርት ከ 50,000- 100,000 ሊትር ነው/

51. እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ዘመናዊ የማሽነሪ ጥገናና እድሳት ስርዓት በመዘርጋት አጠቃላይ የፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀም 90% የደረሰ መሆኑን ያረጋገጠና አጠቃላይ የፋብሪካ የጊዜ አጠቃቀም ከ87% እንዳይወርድ ድጋፍ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣
52. ከላይ በተጠቀሱት የፋብሪካ ጊዜያት አጠቃቀም ምክንያት የኢታኖል ፕላንቱ ለምርት ሂደት የሚያስፈልገውን የእንፋሎት ሃይል ማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት፡-

- በ 2006 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 256 የምርት ቀናት በእቅድ ተይዞ 217.38 ሥራ ላይ ከዋሉ የምርት ቀናት በእንፋሎት ሃይል መቆራረጥ ለ 16.50 ቀናት የኢታኖል ፕላንቱ ማምረት ያቆመ መሆኑ ታውቋል፡፡/የጊዜ አጠቃቀም 78.5%/

- በ 2007 በጀት ዓመት በእቅድ ከተያዘ 257.6 የምርት ቀናት 203.4 ቀናት ሥራ ላይ በመዋል ለ 22.1 ቀናት ምርት ማምረት ያልተቻለ መሆኑ/የጊዜ አጠቃቀም 70.4%/ ሲገለፅ፤ በ 2008 በጀት ዓመት በእቅድ ከተያዘ 182 ቀናት ሥራ ላይ የዋለ 101.32 ቀናት በመሆኑ/የጊዜ አጠቃቀም 55.7%/፤ፋብሪካው ምርት ማምረት ከጀመረበት ህዳር/2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዚያ/2008 ዓ.ም ወር ድረስ ለሁለት ወራት መቆሙ የሚታወቅ ሲሆን፤በተጨማሪም በስኳር ፋብሪካው ቦይለር ተደጋጋሚ ብልሽት ምክንያት እ.ኤ.አ ከ 05/04/2016 ጀምሮ የኦዲቱ ቃለ-መጠይቅ መልስ እስከ ተሰጠበት 06/10/2008 ዓ.ም ድረስ ቆሞ በአካል የታየ መሆኑ ታውቋል፡፡

53. ስለሁኔታው የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅና የኢታኖል ፕላንት ምርት ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የፋብሪካ ኃላፊው የታንደም ቢ ወፍጮ ቁጥር 1 ተርባይን በእርጅና ምክንያት ከሥራ መስመር ከ 2006 ዓ.ም ጀምሮ በመውጣቱ ችግሩን ለመቅረፍ በማኔጅመንት ታምኖበት አዲስ የተርባይን ግዥ በ EI 13-7630 ከ FIVES CAIL ካምፓኒ ተገዝቶ ተከላው በሚያዚያ/2008 ዓ.ም ቢደረግም የተርባኑ ዙሪት ከወፍጮው ዙሪት ጋር አንድ ባለመሆኑ ከካምፓኒው ጋር እንዲያስተካክል በሂደት ላይ ያሉ መሆኑን፤ እንዲሁም የመለዋወጫዎች ጥያቄን በተመለከተ በየጊዜው ለኮርፖሬሽኑ ጥያቄዎች ቢቀርቡም በገንዘብ እጥረት ምክንያት እጅግ አስፈላጊ የሚባሉ ብቻ እየተባለ ተመርጠው እንዲገዙ የሚባል ሲሆን፤ያም ቢሆን የውጪ ገንዘብ እስኪፈቀድ ጊዜ የሚወስድበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ሲገልፁ የኢታኖል ፕላንቱ የቡድን መሪ በሰጡት መልስ በስኳር ፋብሪካው ላይ የሚደርስ የመለዋወጫ ችግር የኢታኖል ፕላንቱን የሚፈታተን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

54. የስኳር ኮርፖሬሽኑ ከተሰጠው ተግባር በቂ የቴክኒካል ድጋፍን ክትትል በማድረግ በመስጠት የፋብሪካዎችን ምርታማነት ማሳደግ፣ መደገፍ፣ መከታተልና መቆጣጠር የሚል ቢሆንም የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በምርት ሂደቱ የሚያስፈልጉት መለዋወጫወች በተፈለገው ሁኔታ ባለማግኘቱ ከ 2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን የመለዋወጫ ችግሮች የገጠሙት በመሆኑ ለኢታኖል ፕላንቱ/ፋብሪካ/ ማምረት ሂደት የሚያስፈልግ የእንፋሎት ሃይል ማቅረብ ባለመቻሉ ሀገሪቷ ለተሽከርካሪዎች ነዳጅነት ከ 5-10% በመቀላቀል የምትጠቀምበትን412,139.8 ሊትር በማምረት ብር 3,915,328.10እና ለተለያዩ መጠጥ ኢንደስትሪዎች በግብዓትነት የሚሸጠውን ረክቲፋይድ ስፐሪት አልኮሆል 176,631.4 ሊትር በማምረት ብር 2,559,388.99 በድምሩ ብር 6,474,717.09 እንዳታገኝ አድርጓል፡፡

የማሽነሪ እና የግብዓት አቅርቦት የሥራ መቆም

ችግርን ያቃለለ መሆኑን በተመለከተ

55. የማሽነሪ እና የግብዓት አቅርቦት ድጋፍን ከምርት እቅድ ጋር የተጣጣመ በማድረግ በግብዓት ምክንት የሚፈጠር የሥራ መቆምን/Down Time/ ወደ ዜሮ እንዲወርድ ሊደረግ ይገባል፡፡

56. ኮርፖሬሽኑ የማሽነሪና የግብዓት አቅርቦት ድጋፍ ከምርት እቅድ ጋር የተጣጣመ በማድረግ በግብዓት ምክንያት የሚፈጠር የሥራ መቆምን/Down Time/ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ/ኢታኖል ፕላንት ወደ ዜሮ እንዲወርድ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ:- የመተሐራ ኢታኖል ፕላንት የኢታኖል አልኮሆልና ረክቲፋይድ ስፕሪት አልኮሆል ምርትን ለማምረት የሚያስፈልገውን የእንፋሎት ሃይል የሚያገኘው የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ቦይለር ክፍል በጤናማ/ሳይበላሽ/ ሁኔታ ሲንቀሳቀስ በመሆኑ፤

- በ 2006 በጀትዓመት የምርት ዘመን የቦይለር ቁጥር 2 ቱቦ/የእንፋሎት ሃይል ማመንጫ/በመቀደዱ ቦይለሩ ለጥገና ከሥራ መስመሩ ሲወጣ በተከሰተ የእንፋሎት ሃይል እጥረት ምክንያት የሸንኮራ አገዳ መፍጨትና የስኳር ማምረት አቅም መቀነስ ያጋጠመ መሆኑ፤
- የታንደም ቢ ወፍጮ በተለያዩ ሜካኒካል ችግሮች ከሥራ መስመር እንዲወጣ መደረግ፣
- የ4ኛ ወፍጮ ተይል ባር መሰበር/ ከወፍጮ የሚያገናኝ አካል/፣
- 3ኛ ወፍጮ በተርባይን ጊርና ሮተር/ሃይል አመንጪ/ መበላሸት፣
- 1ኛ ወፍጮ በወኮ ጊር ቦክስ ጥርስ መሸራረፍ/ሃይል ለመጨመርና ለመቀነስ የሚያገለግል/
- 5ኛ ወፍጮ በተርባይን/የወፍጮ አንቀሳቃሽ/ ችግር ምክንያት አለመሥራት፣
- 3ኛ ወፍጮ ተርባይኑ ላይ ባለው ችግር ምክንያት እና 1ኛ ወፍጮ በወኮ ጊር ቦክስ ችግር ምክንያት በአነስተኛ ሀይድሮሊክ/ማንቀሳቀሻ ዘዴ/ እንዲሰሩ በመደረጉ የሚፈለገው የሸንኮራ አገዳ የመጭመቅ አቅም ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ፣
- በዲፊውዘር /የአገዳ መጭመቂያ ክፍል/ ፓወር ተርባይን 3 ቁጥር ከሥራ መስመር መውጣት የተነሳ የሃይል ጫና/ሎድ/ እንዲቀንስ መደረግ፣
- የታንደም ቢ ኤሊቬተር ኬን ኬሪየር/አገዳን የሚያጓጉዝ/ አነሰተኛው ቦርድና ስላት በተደጋጋሚ ብልሽት ምክንያት ጊዜ እንዲባክን ማድረግ፣

57. ፕሮሰስ ሀውስ/የምርት ክንውን ክፍል/ በተመለከተ፡-

- የዲኮንቲነስ ክሪስታላይዘሮች ማቀዝቀዣ/ኩሊንግ ዲስክ/ስኳርን የሚያገላብጥና በውስጡ ማቀዝቀዣ ያለው በእርጅና ምክንያት በተደጋጋሚ ተቀዶ ማፍሰስ፣

- የፓኖች ዲስቻርጅ ቫልቭ ሀይድሮሊክ ሲሊንደር ረበር ካፕ/ስኳር ማስወጫ ክፍልና ይህ እንዲንቀሳቀስ የሚከፈትና የሚዘጋ አካል/ በተደጋጋሚ መበላሸትና ፓኖች ከሥራ መስመር መውጣት የስኳር ምርት መቀነስ፣
- የኦሲ ፊልተሮች/በጭቃ ውስጥ ያለን ስኳር የሚለይ/ ወንፊት ባለመኖሩ ምክንያት ኦሲፊልተሮቹ በቀዳዳ ወንፊቶች መሥራታቸው፣
- የዶርኮ ፓምፖች ጎማ/የወፍጮ ማቀዝቀዣ ዘይቱን የሚሞሉ ፓምፖች/ በተደጋጋሚ መቀደድ ምክንያት ከዶር ክላሪፋየሮች/ጁስን የሚያጣራ አካል/ የጭቃ ማውጣት መቀነስ ምክንያት የጭቃ መወፈር ችግር መከሰት፣
- የናሽ ቫኪዩም ፓምፖች/የአየር ክፍተት እንዲፈጠር የሚረዱ ፓምፖች/ መዳከም፣
- የቫኪዩም ሬጉሌተር ሲስተም/ቫኪዩም በሚፈለገው መጠን መሆኑን መቆጣጠር/ በተደጋጋሚ መበላሸት፣
- የአዲሱ ኦሲ ፊልተር/በጭቃ ውስጥያለን ስኳር የሚለይ/ ወንፊት መደፈንና የኮንደንሰር/የማጠየዣ/ ውሃ በቂ አለመሆን፣

የስኳር ምርት ብክነትን ለመቆጣጠር ባላስቻሉ ምክንያቶች የዓመቱ የምርት ቀናት 259 በእቅድ ተይዞ አፈፃፀሙ 263 የደረሰ ሲሆን፣በእቅድ የተያዘ አጠቃላይ የፋብሪካ የጊዜ አጠቃቀም 88% ሆኖ አፈፃፀሙ 81.9% መሆኑና የሚባክን ሰዓት 12% በእቅድ ተይዞ አፈፃፀሙ 18.1% መሆኑ ታውቋል፡

58. ከላይ በተገለፁት ችግሮች ምክንያት በ 2006 በጀት ዓመት በኢታኖል ፕላንት ማምረት ሂደት ላይ ተፅዕኖ በማረፉ በእንፋሎት ሃይል እጥረት ምክንያት በእቅድ 7,182.70 ኪሎ ሊትር ኢታኖል ለማምረት ታቅዶ ክንውኑ 3,864.79 ኪሎ ሊትር 3,317.91 ኪሎ ሊትር በማነስ መመረት ከቻለባቸው ዋና ምክንያቶች የስኳር ፋብሪካው የሚያስፈልጉትን መለዋወጫዎች ባለማግኘቱ የኢታኖል ፕላንቱ በእንፋሎት ሃይል መቆራረጥ ምክንያት ለ 16.50 ቀናት ምርት ሳያመርት በመቆሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

59. በ2007 በጀት ዓመትም ከላይ በ 2006 በጀት ዓመት የተከሰተው ችግር መፍትሄ ሳያገኝ የቀረ በመሆኑ እና የዲፊውዘር ፕላንት ታንደም ኤ መቆሙ፣ ኤቫፖሬሽንና ቫኪዩም ፕላንት በእንፋሎት ሃይል እጥረት እና በኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥ ምክንያት በተደጋጋሚ ከሥራ መስመር በመውጣታቸው በሙሉ አቅም ባለመሥራታቸው ምክንያት የፋብሪካ የባከነ ሰዓት በመጨመሩ/ወደ 12 ሰዓት ለማውረድ እቅድ ተይዞ ወደ 16.46 ከፍ ያለ መሆኑ የፋብሪካ እለታዊ የስኳር ምርት እቅድ አመራረት በቀን ከ 5,000 ኩንታል ወደ 4,479 ሊወርድ የቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

60. በ2006 በጀት ዓመት የተከሰቱ የመለዋወጫ ችግሮች እንዳሉ በ 2007 በጀት ዓመትም የቀጠሉ በመሆናቸው የፋብሪካው የምርት ቀናት በእቅድ 260 ሆኖ ቢያዝም አፈፃፀሙ 242 ቀናት ሊሆን ችሏል፡፡ በተጨማሪም አጠቃላይ የፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀም 88% የታቀደ ሆኖ አፈፃፀሙ 83.54% መሆኑ ታውቋል፡፡

61. በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በመለዋወጫ እጥረት ምክንያት የተከሰተው በሙሉ አቅም ያለመሥራት ችግር በኢታኖል ፕላንቱ የማምረት ሂደት ላይ በ 2007 በጀት ዓመት የምርት ዘመን 7,300 ኪሎ ሊትር ኢታኖል አልኮሆል ለማምረት ታቅዶ 5,508.0 ኪሎ ሊትር በ 1,792 ኪሎ ሊትር ያነሰ እንዲመረት አድርጓል፡፡ ፕላንቱ በእቅድ 257.6 የምርት ቀናት ተይዞለት 54.2 ቀናት ባነሰ 203.4 ቀናትን ሥራ ላይ ሊያውል የቻለ መሆኑ ሲገለፅ፤ ሥራ ላይ ላልዋሉ ቀናት ዋና ምክንያት ከስኳር ፋብሪካው ማግኘት የሚገባውን የእንፋሎት ሃይል ለ 22.1 ቀናት ማግኘት ባለመቻሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

62. በ 2008 በጀት ዓመት በስኳር ፋብሪካው ላይ የተከሰቱ ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡- የታንደምቢ 1 ቁጥር ወፍጮ ጊር ቦክስ ከ 2006 በጀት ዓመት የምርት ዘመን ጀምሮ በእርጅና ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ በመሆኑ እስከ 2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን ድረስ ባለመተካቱ በአንዱ ቁጥር ወፍጮ የሚሰራው የፕላንቱ 60% የመጭመቅ አቅም በማሳለፍ ዘዴ/ባይ ፓስ/ እንዲሰራ በመደረጉ በሌሎች ወፍጮዎች ላይ ከፍተኛ ጫና በመፍጠር እያደረሰባቸው ያለውን ጉዳት ለመቀነስ በዝቅተኛ አቅም እንዲሰሩ የተደረጉ መሆኑ ሲገለፅ፤ የታንደም ቢ ቁጥር 1 ወፍጮ ከሥራ መስመር መውጣትና የዲፊውዘር በመብራት መጥፋት ምክንያት ከሥራ መስመር መውጣት ከገለባ ጋር የሚባክነውን ስኳር በተገቢው ሁኔታ ማስቀረት ባለማስቻሉ ከገለባው ጋር የሚሄደው ስኳር ቦይለር ላይ በተፈለገው መንገድ ስለማይነድ የቦይለሩን/የእንፋሎት አመንጪ ክፍሉን/ የሥራ ክንውን አቅም ዝቅ የሚያደርግ በመሆኑ የቦይለር ጠረጋ ጊዜን እንዲራዘም በማድረጉ ለስኳር ምርት የሚያስፈልግ የእንፋሎት ሃይል እጥረት እንዲፈጠር ያደረገ መሆኑ በ 2008 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡

63. ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የስኳር ፋብሪካው የዓመቱ የምርት ቀናት እቅድ 253 ሆኖ አፈፃፀሙ በመለዋወጫዎቹ እጥረት ወደ 152 ወርዷል፡፡ አጠቃላይ የፋብሪካ ጊዜ አጠቃቀም 84.17% በእቅድ ተይዞ አፈፃፀሙ 76.98% መሆኑ ታውቋል፡፡

የስኳር ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ ባለመሥራቱ በቂ የእንፋሎት ሃይል በ 2008 በጀት ዓመት ለኢታኖል ፕላንቱ ባለመስጠቱ በምርት አመራረት ሂደቱ ላይ ተፅኖ በማሳደሩ 182 የምርት ቀናት በእቅድ ተይዞ አፈፃፀሙ 80.68 ቀናት በማነስ በአፈፃፀም 101.32 ቀናት ያመረተ መሆኑ ሲገለፅ፤ ከሚያዚያ ወር በኋላ ባሉት ጊዜያት ፕላንቱ ሙሉ በሙሉ ማምረቱን

ያቆመ ሲሆን፣ለዚህም ዋናው ምክንያት የስኳር ፋብሪካው ቦይለር በተደጋጋሚ በመበላሸቱ ለፕላንቱ የሚቀርበው የእንፋሎት ሃይል እጥረት በመከሰቱ መሆኑ ታውቋል፡፡

64. ስለሁኔታው የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅና የኢታኖል ፕላንት ምርት ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የፋብሪካ ኃላፊው በግዥ መጠይቅ EI 13-7156 Complete Overhauling of Extraction Plant & Diffuser Plant Equipments & machineries/የአገዳ መጭመቂያ ክፍሎችን የተሟላ እድሳት ማድረግ/ እና በግዥ መጠይቅ EI 13-7155 Complete Overhauling of Service of boiler plant equipment & machineries/የእንፋሎት አመንጪ ክፍሎችን ማደስ/ ጥያቄዎችን በማቅረብ ግዥዎቹ እንዲከናወኑ ተፈቅዶ የግዥ ሂደቱ የተከናወነ ሲሆን፤ በዚህ መሰረት በ EI 13-7155 ለተጠየቀው ሰርቪስ ጆይቲ ሱገር ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ካምፓኒ/Jyoti Sugar Engineering pvt.ltd/ ሥራዎችን በፕሮጀክትነት ይዘው እንዲሰሩ መደረጉን ሲገልፁ፤የኢታኖል ፕላንቱ የምርት ቡድን መሪ በስኳር ፋብሪካው ቦይለር በተደጋጋሚ ብልሽት ምክንያት ማምረት ማቆም የተደረሰ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

65. የፋብሪካው ኃላፊ የፋብሪካው ዋና ክፍሎች ችግር መፍትሄ እንዲያገኝ ለጆይቲ ሱገር ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ካምፓኒ የተሰጠ መሆኑን ቢገልፁም ችግሮቹ የኦዲቱ ቃለ-መጠይቅ እስከ ቀረበበት 24/09/2008 ዓ.ም ድረስ ያልተቃለሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

66. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር የማሽነሪ፣ የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ መስጠት፤ሀብትን አዛውሮ መጠቀም፣ ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ ግብዓቶችን በወቅቱ እንዲቀርቡ ማድረግ ከሚለው አንፃር የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የመለዋወጫ አቅርቦት ባለማግኘቱ ለተደጋጋሚ ጊዜ የቦይለር/የእንፋሎት ሃይል ማመንጫ ክፍሉ/ ለብልሽት በመጋለጡ ምክንያት በተሟላ አቅሙ ባለመሥራቱ በየዓመቱ ከእቅድ በታች ስኳር አምራች ሆኖ በኢታኖል ፕላንቱ/ፋብሪካው/ ላይ ተፅዕኖ በማሳደሩ ኢታኖል አልኮሆል በተሟላ አቅሙ እንዳያመርት በማድረግ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚያበረክተውን አስተዋፆ ያነሰ አድርጎታል፡፡

ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት ወጪ

ቆጣቢ በሆነ መልኩ መፈፀማቸውን በተመለከተ

67. ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ሊፈፀሙ እና የግዥ ፈፃሚ አካላት ከግዥ ጋር ለሚወስኗቸው ውሳኔዎች ኃላፊና ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊደረግ እንዲሁምከአቅራቢዎች ጋር ለሚመሰረት ዘላቂ ግንኙነቶች ግብዓት እንዲሆን የገበያ ጥናት ሊከናወንይገባል፡፡
68. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ውጤታማነት ግዥዎችን ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት፤እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በአግባቡ የተፈፀሙ መሆኑን የተከታተለና የተቆጣጠረ፣ የግዥ ፈፃሚ አካላት ከግዥ ጋር ለሚወስኗቸው ውሳኔዎች ኃላፊና ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደረገ እንዲሁም ከአቅራቢዎች ጋር ለሚመሰረት ዘላቂ ግንኙነቶች ግብዓት እንዲሆን የገበያ ጥናት እንዲከናወን ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የተከናወኑ ግዥዎች በሚከተለው ሁኔታ ተፈፅመው ተገኝተዋል፡፡
69. በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ለጥገና ሞኤንኮ የገባ ፎርክ ሊፍት እንዲመለስ በቁጥር 23/06/4.1 በቀን 27/03/06 ለኢትዮጵያ የሞተርና የመሀንዲሶች ማህበር ከተፃፈ ደብዳቤ የፎርክ ሊፍት የጥገና ዋጋ ብር 818,489.55/ ስምንት መቶ አስራስምንት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ከ 55/100/ የተጠየቀ ሆኖ ለዚህም ሥራ ቅድመ-ክፍያ ብር 28,807.50/ ሃያ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሰባት ከ 50/100/ መከፈሉ ተገልፆ የተጠየቀው የገንዘብ መጠን እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ቅድሚያ የተከፈለው ብርና ለጥገና የተሰጠው ፎርክ ሊፍት በገባበት መልኩ ይመለስ የሚል ደብዳቤ መመልከት የተቻለ መሆኑና ይህም የግዥ ሁኔታ ክርክር ያስነሳ ሆኖ በ 2008 በጀት ዓመትም ውሳኔ ያላገኘ መሆኑ ማወቅ ተችሏል፡፡
70. በግዥ መጠይቅ ቁጥር MSD/15038 የሥራ መከላከያ አልባሳት/Gown,T-Shirt and Trousers/ ግዥ እንዲከናወን ተጠይቆ በግልፅ ጨረታ የወጣው አሸናፊ ሀና ዘሪሁን የፅህፈት መሳሪያዎችና አላቂ እቃዎች ንግድ ሥራ የግል ኢንተርፕራይዝ ለአልባሳቱ ብር 555,722.61 ለ 60 ቀናት የሚቆይ የሰጠ ቢሆንም፤የጊዜ ገደቡ በማለፉ ምክንያት አስበሞ ከሚባል የ 2ኛ ደረጃ አሸናፊ ድርጅት በብር 724,557.50 ግዡው እንዲከናወን በመደረጉ ድርጅቱ ተጨማሪ ወጪ በመክፈል ብር 168,834.89 እንዲያወጣ የተደረገ መሆኑ ከውስጥ ኦዲት ሪፖርት መረዳት ተችሏል፡፡
71. በግዥ ቁጥር MSD/1509 3700 Normal Overhaul /የሰራተኞች ዩኒፎርም/ እንዲገዛ ተጠይቆ በግልፅ ጨረታ በመውጣቱ በቀን 24/12/2005 የተከፈተ ሆኖ አስበሞ ኢንደስትሪል ኃ/የ/ግ/ማህበር ቫትን ጨምሮ በብር 705,266.25 ያቀረበ ቢሆንም በወቅቱ ግዥው ባለመከናወኑ በሌላ ጊዜ ከአዳማ ጋርመንት ቫትን ጨምሮ በብር 1,178,635.00 እንዲገዛ በመደረጉ ድርጅቱ በተመሳሳይ ግዥ ላይ ብር 437,368.75 ተጨማሪ ወጪ እንዲከፍል የተደረገ መሆኑ ከውስጥ ኦዲት ሪፖርት ማወቅ ተችሏል፡፡

72. እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ የግዥ ፈፃሚ አካላትና ሰራተኞችን ከግዥ ጋር በተያያዘ ለሚወስኗቸው ውሳኔዎች ኃላፊና ተጠያቂ ማድረጉን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ የኮርፖሬሽኑ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በ 2007 በጀት ዓመት ካቀረበው ሪፖርት በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በ 2006 በጀት ዓመት የግዥ ሂደትና አሰራርን በተመለከተ፡-

- በEI No 13-7123, 13-6886, 13-7158, 13-7204, 13-7263/67 የተፈፀሙ ግዥዎች በውል ያልታሰሩና የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ያልተያዘላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

73. በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ውጤታማነት ለሚከናወኑ ግዥዎች፤እንዲሁም ከአቅራቢዎች ጋር ለሚመሰርታቸው ዘላቂ ግንኙነቶች ግብዓት እንዲሆን የኮርፖሬሽኑ ግዥ ፈፃሚ አካላት የገበያ ጥናት ያከናወኑ ስለመሆናቸው ክትትል ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ለፋብለሪካው የሚገዙ መለዋወጫዎችም ሆነ አስፈላጊ እቃዎች በዓመታዊ እቅድ ውስጥ ተካተው የሚገኙትን ለመግዛት ሲፈልግ ድርጅቱን ተጠቃሚ ለማድረግ ቅድመ-የገበያ ጥናት የሚያደርግ ስለመሆኑ ከ 2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት ዓመት የተደረጉ ቅድመ-ጥናቶች ስለመኖራቸው በኦዲት ቡድኑ ለግዥ ቡድን ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የገበያ ጥናት በኮርፖሬሽን ማርኬቲንግ ክፍል የተቋቋመ ቢሆንም፤ከዚህ ክፍል የደረሳቸው መመሪያ የሌለ በመሆኑ በራሳቸው አሰራር ዘዴ የሚጠቀሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

74. ስለሁኔታው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የግዥ ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ሞኤንኮ ለጥገና የገባ ፎርክ ሊፍትን በተመለከተ ዋጋው የተጋነነ በመሆኑ እቃው ባለበት ሁኔታ እንዲመለስ በደብዳቤ ቁጥር 23/06/4-1 በቀን 27/03/ 2006 የተጠየቀ ቢሆንም ተጨማሪ ብር 2415 እንዲከፈል በማለት በዋጋ ማቅረቢያ ፕሮፎርማ/PRF 057163 በቀን እ.ኤ.አ 03/12/2013 የሰጡ በመሆኑ ለዚህ ማብራሪያ ተጠይቆ በደብዳቤ መልስ የሚሰጡ መሆኑን በመግለፃቸው ይህ ባለመደረጉ በቅርቡ በግንባር ቀርበው በመጠየቃቸው መልስ እየተጠባበቁ ለመሆኑ በ 2006 በጀት ዓመት ለተከናወነ ድርጊት ለኦዲቱ መልስ እስከተሰጠበት 8/10/2008 ዓ.ም ድረስ ውሳኔ ያላገኙና በመጠባበቅ ላይ ያሉ መሆኑን ገልፀው የግዥ ሂደቱ በግዥ መመሪያ መሰረት ከአንድ ብቸኛ አቅራቢ በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

75. የሥራ መከላከያ አልባሳትን ግዥ በተመለከተ በወቅቱ የግዥ ቡድን ኃላፊዎችና ሰራተኞች በህግ ጥላ ስር ስለነበሩና ሥራውን በአግባቡ አስረድቶ ወደ መስመር ለማስገባት የባለሙያ ችግር ስለነበረና የሰው ሃይል እጥረት በማጋጠሙ ብዛት ያላቸውን ጥያቄዎች ከማስተናገድ አንፃር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት የማስፈፀም ሂደት ውስጥ ጊዜው በመራዘሙና ዋጋው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ በማለፉ ምክንያት አቅራቢው ሲጠየቅ ዋጋ በመጨመሩ ወደ ሁለተኛው አሸናፊ መሄድ ግድ ሆኖ በመገኘቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

76. እንዲሁም ኖርማል ኦቨር ሆል/የሰራተኛ ዩኒፎርም/ ቱታ ግዥን በተመለከተ ግልፅ ጨረታ ወጥቶ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት ከተለየ በኋላ እንደገና ግዥው በቀጥታ ከአዳማ ጋርመንት እንዲገዛ የተደረገበት ምክንያቶች፡-

- በወቅቱና በተሻለ ጥራት ሥራዎችን ሳይንጠባጠቡ ማቅረብ እንደሚችል በመረጋገጡ
- ትልቅ አቅም ስላለው ያለንን ፍላጎት በተፈለገው መጠን ያቀርባል ተብሎ ስለታመነበት

- የመንግስት ድርጅት በመሆኑ ካለን ገንዘብ እጥረት አኳያ በአከፋፈል እረገድ እቃውን ከተረከብን በኋላ በሁለት እና ሶስት ጊዜ ስለሚፈቅድ
- እንዲሁም በተለየ ሁኔታ የመከላከያ አልባሳት ግዥ ላይ በጨረታ የሚያሸንፉ የግል ድርጅቶች በአስተማማኝ ሁኔታ ለማቅረብ የሚቸገሩና በተንጠባጠበ መልኩ ስለሚያስረክቡ በሰራተኞች በኩል ቅሬታዎች እየቀረበብን በመምጣታቸው ለአሰራር ችግር በመፍጠሩ ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

77. የግዥ ፈፃሚ አካላት ለወሰኑአቸው ግዥዎች ተጠያቂ መደረጋቸውን በተመለከተ ያለውልና ውል ማስከበሪያ የተፈፀሙ ግዥዎች ለሚለው በሰጡት መልስ የግዥ መጠይቅ ቁጥር 13-7126 /የግዥ ትዕዛዝ ቁጥር 1392/FM በወቅቱ ግዥው ሲፈፀም የውል ማስከበሪያ የተያዘ ሲሆን ውልን በተመለከተ የግዥ ትዕዛዙ ላይ በአግባቡ ተዘርዝረው የተቀመጡ እንደውል ማሰሪያ ጥቅም ላይ የሚውሉ ማሰሪያ ነጥቦች አብረው የተሰጡ በመሆናቸው እቃውን መረከብ የተቻለ መሆኑ፣
    - የግዥ መጠይቅ ቁጥር 13- 6886 / የግዥ ትዕዛዝ ቁጥር 1421/ FM/ በውስን ጨረታ የተፈፀመ በመሆኑ የውል ማስከበሪያ ያልተያዘለት ሲሆን፤ ውልን በተመለከተ ከግዥ ትዕዛዝ ጋር እንደ ውል ጥቅም ላይ የሚውል ሃላፊነት፣ተግባርና ግዴታን የሚገልፅ ተያይዞ በመቅረቡ እቃዎችን መረከብ የተቻለ መሆኑ፣
    - በግዥ መጠይቅ ቁጥር 13-7158 /የግዥ ትዕዛዝ ቁጥር 1551/ FM/
13-7204 /የግዥ ትዕዛዝ ቁጥር 1552/ FM/
13-7263 /የግዥ ትዕዛዝ ቁጥር 1441/ FM/

ከላይ የተጠቀሱትን የግዥ መጠይቆች በተመለከተ ከዚህ ቀደም እነዚህን እቃዎች ለመግዛት ከቀጥታ አቅራቢ ግዥው ይፈፀም የነበረ ሲሆን፤ነገርግን የገበያና የአቅራቢ አማራጭ ሊገኝ ይችላል በሚል ግልፅ ጨረታ ወጥቶ ሆኖም ከዋናው አቅራቢ ውጪ ሊገኝ ባለመቻሉ የውል ማስከበሪያ አልተጠየቀም፤ ይሁን እንጂ ውልን በተመለከተ ከግዥ ትዕዛዝ ጋር ኃላፊነት፣ ተግባርና ግዴታን የያዘ ዝርዝር አባሪ በማድረግ እቃዎችን መረከብ የቻሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

78. የገበያ ጥናት የሚደረግ ስለመሆኑ በሰጡት መልስ የቅድመ-ገበያ ጥናት የሚያጠና በኮርፖሬሽን የተቋቋመ ማርኬቲንግ/የንግድ/ ክፍል ያለ ሲሆን፤ ስለጥናቱ የተጠቃለለ ሪፖርት ያላገኘን ሲሆን፤ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ እየሰራንበት ባለው አሰራር የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃዎችን የምናገኘው ከዚህ በታች በቀረቡት አግባብ ነው፡፡
    - ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ እቃዎች የተገዙበት ሰነድ በማየት፤
    - ከእህት ኩባንያዎች /ፈንጫና ወንጂ/ ቀድመው ወይም በቅርብ ጊዜ የገዙበትን ዋጋ በመጠየቅ፣
    - ዓለም አቀፍ የዋጋ ኢንዴክሶችን ከድህረ ገፅ ላይ በመመልከት፣

- የሀገር ውስጥ የገበያ ዋጋዎችን በአካል የተለያዩ ቦታዎች ሄዶ በመጠየቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

79. የግዥ ቡድን ኃላፊው የሥራ መከላከያ፣ የሰራተኛ ዩኒፎርም እና በተለያ የግዥ መጠይቅ ቁጥር የቀረቡ ግዥዎችን ከወቅታዊ የባለሙያ ችግር፣ ከወጥ አቅራቢነት እና እንደ ውል የሚያገለግሉ ግዴታና ሃላፊነትን የሚዘረዝሩ ሰነዶች በማያዥ እቃዎችን የተረከቡ መሆኑን ቢገልፁም፤ የሥራ መከላከያና የሰራተኛ ዩኒፎርምን በተመለከተ ድርጅቱ አላግባብ ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ የተረደገባቸው በመሆኑ ወጪ ቆጣቢነት ከሚለው አኳያ በኦዲት ቡድኑ ተቀባይነት ያላገኙ ሲሆን ውልን በተመለከተም በቀጥታ ውል መዋዋል ሲቻል እንደ ውል የምንጠቀምበትን አያይዘን በመላክ እቃዎችን መረከብ ችለናል የሚለውም ሀሳብ አሳማኝ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

80. በስኳር ኮርፖሬሽን ግዥና ንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ተግባር ምንም ዓይነት ተገቢ የሆነ ቅሬታ የማይቀርብበት የጨረታ ሂደት ማከናወን እና በውሉ በተመለከተው ጊዜ ግዥ ማጠናቀቅ፤እንዲሁም በስኳር ኮርፖሬሽኑ ግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሐምሌ 2003 አንቀጽ 28.2 መሰረት በኮርፖሬሽኑና በአቅራቢው መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም ከሚለው አንፃር ተግባራዊ ባለመደረጉ የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በተፈፀሙ ግዝዎች ያልተገባ ተጨማሪ ወጪዎች እንዲያወጣ ተደርጓል በተጨማሪም በውል ያልታሰረ ግዥም እንዲፈፅም ተደርጓል፡፡

የግዥ ፍላጎት በመርሀ-ግብር ተደግፎ

የሚፈፀም መሆኑን በተመለከተ

81. የኮርፖሬሽኑ አካላት የታቀዱ የሥራ ፕሮግራማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ግዥ በወቅቱ ለመፈፀም የሚያስችል በመርሀ-ግብር የተደገፈ የግዥ ፍላጎት እንዲዘጋጅ መመሪያ ሊሰጥ ይገባል፡፡

82. ኮርፖሬሽኑ የኮርፖሬሽኑ አካላት የታቀዱ የሥራ ፕሮግራማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ግዥበወቅቱ ለመፈፀም የሚያስችል በመርሐ-ግብር የተደገፈ የግዥ ፍላጎት በወቅቱ እንዲያዘጋጁ መመሪያ የሰጠ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ - በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ግዥዎች በመርሐ ግብር የተደገፉ ቢሆንም ከግዥ አፈፃፀም ጋር በተዛመደ የሚከተለው ችግር ተስተውሏል፡፡

- የመተሐራስኳርፋብሪካበቀን 25/03/2006 ዓ.ም ለስኳር ኮርፖሬሽን ደረቅ ወደብ ላይ ረጅም ቀናት ያስቆጠሩ ኮንቴይነሮችን በተመለከተ በተፃፈ ደብዳቤ በሰጠው መልስ ሶስት ኮንቴይነሮች፡-
    - APZU3598425
    - APHU6890865
    - GESU559759
- በገንዘብእጥረትምክንያትበጉምሪክ መጋዘን የሚገባ ግዴታ መሟላት ባለመቻሉ በሞጆ ደረቅ ወደብ የሚገኙ መሆኑን በመግለፅ ወደ ፋብሪካ ማድረስ ያልቻለ መሆኑን ከደብዳቤው መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም በገንዘብ እጥረት የተከሰተ ችግር መሆኑ ተገልጿል፡፡

83. ስለ ሁኔታው የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የግዥ ቡድን በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ግዥዎች በሙሉ በእቅድና በበጀት ላይ የተመሰረቱ ሆነው የሚዘጋጁት የገንዘብ አቅርቦቱ ከስኳር ኮርፖሬሽን እንደሚመቻች ግንዛቤ ተወስዶ ሲሆን፤ ይሁን እንጂ ለወደብ ማስለቀቂያ ገንዘብ በሚጠየቅበት ጊዜ የምላሽ መዘግየት በመፈጠሩ የወደብ ቆይታ ጊዜው የተራዘመ ሆኗል፡፡ሆኖም የተጠቀሱት ኮንቴይነሮች የግዥ ትዕዛዝ ቁጥራቸው 1023/FM እና 1392/FM የጉምሩክ ጉዳያቸው ተጠናቆ ወደ ፋብሪካ ደርሰው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

84. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋይናንስ ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር ሁሉንም የመንግስት ግዴታዎች መከፈል ካለበት ቀን በ 10 ቀን ቀድሞ በትክክልና ያለምንም ቅጣት መክፈል ከሚለው አኳያ ያልተተገበረ በመሆኑ ኮንቴይነሮቹ ከተወሰነላቸው ጊዜ ገደብ ቆይታ መራዘም ምክንያት ያልተገባ ወጪ/ዲመሬጅ/ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚፈፀም ግዥ በቂ የስርጭት ሽፋን መጠቀሙን በተመለከተ

85. ኮርፖሬሽኑ በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ለሚፈፀም ግዥ የጨረታ ጥሪ በቂ የስርጭት ሽፋን ባለውና የውጭ ተጫራቾችን ሊጋብዝ በሚችል ጋዜጣ ላይ ማውጣት፤ በተጨማሪም በርካታ ተጫራቾችን ለማግኘት እንዲቻል በኮርፖሬሽኑ ድረ-ገፅ ላይ በማውጣት እና ለኢምባሲዎች የጨረታው ጥሪ እንዲተላለፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

86. ኮርፖሬሽኑ በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ለሚፈፀም ግዥ የጨረታ ጥሪ በቂ የስርጭት ሽፋን ባለውና የውጭ ተጫራቾችን ሊጋብዝ በሚችል ጋዜጣ ላይ ማውጣት፤በተጨማሪም በርካታ ተጫራቾችን ለማግኘት እንዲቻል በኮርፖሬሽኑ ድረ-ገፅ በማውጣት እና ኢምባሲዎች የጨረታው ጥሪ እንዲተላለፍ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የኢታኖል ተርንኪ/የፋብሪካ ግንባታና ተከላ ሰርቶ የፍተሻ ሙከራ አከናውኖ ማስረከብ/ ፕሮጀክት የጨረታ

ሂደት በቂ የስርጭት ሽፋን ባለው በኢትዮጵያን ሄራልድ የእንግሊዘኛ ጋዜጣ በተለያዩ ጊዜያት መውጣቱ ቢገለፅም፣ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

87. ስለ ሁኔታው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የግዥ ቡድን በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በወቅቱ የስኳር ኮርፖሬሽን ያልተቋቋመ በመሆኑ ድረ-ገፅ ላይ ያልወጣ ሲሆን፣ የዓለምን ተጫራቾች ሊጋብዝ እንደሚችል ከበርካታ ዓመታት ልምድ በተወሰደለት በኢትዮጵያን ሄራልድ የእንግሊዘኛ ጋዜጣ በተለያየ ጊዜ እንዲወጣ የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

88. ማስረጃ የዕውነታ መሰረት ሆኖ መረጃ በተፈለገው ወቅት እንዲቀርብበት ባለመደራጀቱ ምክንያት ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑ የጨረታ ጥሪው በተፈለገው መንገድ ብዙ ተጫራቾችን አሳትፎ ስለመካሄዱ አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

ቋሚ ንብረት ገቢ ከመደረጉ በፊት የንብረቱ ዓይነት

የተፈቀደው ስለመሆኑ መረጋገጡን በተመለከተ

89. ኮርፖሬሽኑ አንድ ቋሚ ንብረት ገቢ ለማድረግ ከመመዝገቡ በፊት የንብረቱ ዓይነትና ጥራት በተፈለገው፣እንዲሁም በተፈቀደው መሰረት መሆኑን የግዥ መጠየቂያ ሰነድን ከአቅራቢው የሽያጭ ፋክቱር ኢንቮይስ ጋር በማመሳከርና አካላዊ ምርመራ/Physical Inspection/ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ቴክኒካል ምርመራ ለሚያስፈልጋቸው ንብረቶች በባለሙያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

90. ኮርፖሬሽኑ አንድ ቋሚ ንብረት ገቢ ለማድረግ ከመመዝገቡ በፊት የንብረቱ ዓይነትና ጥራት በተፈለገው፣እንዲሁም በተፈቀደው መሰረት መሆኑን የግዥ መጠየቂያ ሰነድን ከአቅራቢው የሽያጭ ፋክቱር ኢንቮይስ ጋር መመሳከሩንና አካላዊ ምርመራ/Physical Inspection/ መደረጉን የተከታተለ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ አዲስ ተገዝቶ የተተከለ ቦይለር ፊድ ዋተር አናላይዘር/ለእንፋሎት ሃይል ማመንጨት የሚያስፈልገውን ውሃ የሚያጣራ/ ብር 1,906,362/ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ስድሳ ሁለት/ ለግዥ፣ለመጓጓዣና ከህንድ አገር ለመጡ ባለሙያዎች ለተለያየ ወጪ የተከፈለበትና በሀገር ውስጥ ለተከናወኑ ተግባራት ወጪ የወጣበት ተከላና ኮሚሽኒንግ/የብቃት ፍተሻ/ ተካሂዶለት ከነባሩ ቴክኖሎጂ ጋር ባለመግጠሙ ምክንያት ከተተከለበት ቀን አንስቶ እስከ ኦዲቱ ወቅት ሰኔ/2008 ዓ.ም ከሁለት ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጥ የተቀመጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

91. የታንደም ቢ ወፍጮ ቁጥር 1 ተርባይን በእርጅና ምክንያት ከሥራ መስመር በመውጣቱ በስኳር ማምረት ሂደት ላይ የፈጠረውን ተፅዕኖ ለማቃለል በማኔጅመንት ታምኖበት አዲስ ተርባይን ግዥ በ EI 13-7630 ተጠይቆ የግዥ ሂደቱ በዩሮ 420,007.20 ተከናውኖ FIVES CAIL/ ፋይቭስ ኬል/ ካምፓኒ /የታንደም ቢ ወፍጮዎች ቲ-38 ተርባይን ብቸኛ አምራች፣አቅራቢና ተከላውን ያከናወነ/ ተርባይኑን አምጥቶ በሚያዚያ/2008 ዓ.ም ተከላውን ያከናወነ ቢሆንም፣ የተርባይኑ አዟዟር/ዙሪት

ከወፍጮ አዟዟር ጋር አንድ ባለመሆኑ በስኳር/ኢታኖል ማምረት ሂደት ላይ ችግር የፈጠረ መሆኑ ታውቋል፡፡/ሁለቱም የእስፔስፊኬሽን ችግሮች መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡/

92. በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ እ.ኤ.አ 2013/2014 በጀት ዓመት ብር 2,743,242.00 የሚያወጡ ግዥዎች የክሌም ጥያቄ 1. በእስፔስፊኬሽን/የተጠየቀው እቃ/ 2. በስህተት ርክክብ እቃ ሲቆጠር ማነስ ወይም መብለጥ /ሮንግ ደሊቨሪ/ 3. በመጓጓዝ ወቅት ጉዳት የደረሰባቸው ጥያቄ/ክሌም/ ቀርቦባቸው ደብዳቤ በመፃፃፍ እስከ እ.ኤ/አ 2015/2016 በተደረገ ጥረት ብር 480,533.67 ማስመለስ የተቻለ ሲሆን ብር 226,2708.33 ያልተመለሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

93. ስለ ሁኔታው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የፋብሪካ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የግዥ ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የፋብሪካ ኃላፊው ቦይለር ፊድ ዋተር አናላይዘር/ለእንፋሎት ሃይል ማመንጨት የሚያስፈልገውን ውሃ የሚያጣራ/ እና የታንደም ቢ ወፍጮ ቁጥር 1 ተርባይን በተመለከተ ቦይለር ፊድ ዋተር አናላይዘር ከህንድ አገር ተገዝቶ ባቅራቢው ድርጅት ባለሙያዎች ተገጥሞ ኮሚሽኒንግ ቢደረገም መሳሪያው የሚያነበው እስከ 5 Parts Per Million/ ከአንድ ሚሊዮን 5 ክፍልፋዮችን በማንበቡ/ በአንፃሩ የድርጅቱ ውሃ ማጤዣ/ኮንደንሴት/ እስከ 200 Parts Per Million በመሆኑ አንዳንድ መለወጥ ያለባቸው ዩኒቶች መለወጥ ያለባቸው መሆኑን በመረዳት መሳሪያውን ካቀረበውና ከተከለው ካምፓኒ የምክር አገልግሎት እንዲሰጥ ተጠይቆ በመጠባበቅ ላይ ያሉ መሆኑን ገልፀው የታንደም ቢ ወፍጮ ቁጥር 1 ተርባይን፣ የተርባይኑ ዙሪት ከወፍጮ ዙሪት ጋር አንድ ባለመሆኑ ይህን እንዲያስተካክል ከካምፓኒው ጋር ቀጣይ ሂደቶች እየተደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

94. የግዥ ቡድን መሪው የክሌም ጥያቄዎችን በተመለከተ ምላሽ ላላገኙት ክትትል በማድረግ ምላሽ ለማግኘት የግዥ ክፍሉ ጥረት እያደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

95. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ ከተሰጠው ኃላፊነት ከምርት እቅድ ጋር የተጣጣመ የግብዓት አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ በግብዓት ምክንያት የሚፈጠርን የሥራ መቆምን ወደ ዜሮ ማድረስ ከሚለው አንፃር ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ባለመተግበሩ ለመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶባቸው የመጡ መለዋወጫዎች በትዕዛዝ መሰረት ባለመቅረባቸው በስኳር ፋብሪካው የስኳር እና በኢታኖል ፕላንት ኢታኖል አልኮሆል ማምረት ሂደት ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ዓመታዊ የምርት እቅዳቸው ግቡን እንዳይመታ ከመደረጉም በላይ ክሌም የተጠየቀባቸውም መለዋወጫዎች ወቅታዊ ክትትል ያልተደረገባቸው በመሆኑ ከፍተኛ ገንዘብ እንዳይመለስ ተደርጓል፡፡

ዓመታዊ የንብረት ቆጠራን /Inventory/ን በተመለከተ

96. በንብረት ቆጠራ ወቅት የታዩ ልዩነቶች የንብረት መዝገቡ፣ የእቃዎች መቀበያ ሰነድ፣ በእቃ መጠየቂያ እና በእቃ ማውጫ ሰነድ እና በትክክለኛው ቀሪ ክምችት መካከል ተገቢው ማጣራት ተከናውኖ ልዩነቶች ከተረጋገጡ በኋላ በገበያ ዋጋ መሰረት ተሰልቶ እንዲከፈል ወይም ንብረቱ እንዲተካ ሊደርግ ይገባል፡፡

97. ኮርፖሬሽኑ በንብረት ቆጠራ ወቅት የታዩ ልዩነቶች የንብረት መዝገቡ፣የእቃዎች መቀበያ ሰነድ፣በእቃ መጠየቂያ እና በ እቃ ማውጫ ሰነድና በትክክለኛው ቀሪ መካከል ተገቢው ማጣራት ተከናውኖ ልየነቶች ከተረጋገጡ በኋላ በገበያ ዋጋ ተሰልቶ እንዲከፈል ወይም ንብረቱ እንዲተካ ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ እ.ኤ.አ 2012/2013 እና 2013/2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ወቅት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ንብረቶች/Missing Items/ ያልተገኙ በሚል በቋሚ ንብረት መዝገብ ላይ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡

- 1.ፒክ አፕ/Pick-up/ የሥራ ክፍል ፕላንቴሽን ክላስ ኮድ 5 ሰብ ክላስ ኮድ 5.1 2012/2013 የተቆጠረ 14 ሆኖ በ 2013/2014 ቆጠራ 8 በመገኘቱ 6 በማነስ የተመዘገበ፣
- 2. ሞተር ሳይክል የሥራ ክፍል ፕላንቴሽን ክላስ ኮድ 5 ሰብ ክላስ ኮድ 5.2 በ 2012/2013 የተቆጠረ 80 ሆኖ በ 2013/2014 66 በመቆጠሩ በማነስ 14 የተገኘ፣
- 3.ትራክተር የሥራ ክፍል ፕላንቴሽን ክላስ ኮድ 6 ሰብ ክላስ ኮድ 8.1 በ 2012/2013 የተቆጠረ 16 ሆኖ 2013/2014 9 በመቆጠሩ በማነስ 7 የተገኘ፣
- 4. ትራክተር ኤም ኤስ ኤፍ/MSF/ 290 የሚገኝበት የሥራ ክፍል ቴክኒካል ክላስ ኮድ 8 ሰብ ክላስ ኮድ 8.1 በ 2012/2013 የተቆጠረ 7 ሆኖ 2013/2014 ቆጠራ 1 ብቻ በመገኘቱ በ 6 ያነሰ መሆኑ፣
- 5. ግራይንዲንግ ማሽን የሥራ ክፍል ቢልዲንግ ክላስ ኮድ 3 ሰብ ክላስ ኮድ 3.5 በ 2012/2013 2 የተቆጠረ ሆኖ በ 2013/2014 ያልተገኘ በመሆኑ በ 2 አንሶ መገኘቱ፣
- 6. ኬን ሎደር/ Cane Loader/ የሥራ ክፍል /ሀርቨስቲንግ/ ክላሰድ ኮድ 8 ሰብ ክላስ ኮድ 8.3 በ 2012/2013 23 የተቆጠረ ሆኖ በ 2013/2014 12 በመቆጠሩ በ 11 ያነሰ መሆኑ፣
- 7. ሎው ቤድ/Low bed/ የሥራ ክፍል ኤልፒሲድ/የእርሻ ክፍል/ ክላስ ኮድ 8 ሰብ ክላስ ኮድ 8.8 በ 2012/2013 የተቆጠረ 1 ሆኖ በ 2013/2014 ያልተገኙ በመሆኑ በ 1 ማነስ የተመዘገበ መሆኑ ሲታወቅ፤ አልተገኙም ተብለው በቆጠራ ሰነድ ለተመዘገቡት ንብረቶች የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

98. በተጨማሪም በ 2006 በጀት ዓመት ንብረት ቆጠራ የኢታኖል ምርትን በተመለከተ በታንከር ውስጥ የሚገኙ የሬክቲፋይድና የኢታኖል አልኮሆል መጠን ካሊብሬት ባለመደረጉ ምክንያት ትክክለኛ መጠናቸውን ለማወቅ ያልተቻለ መሆኑ ከ 2007 በጀት ዓመት በኮርፖሬሽኑ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ሪፖርት የተመለከተ በመሆኑ ስለሁኔታው የኦዲት ቡድኑ ለንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ታንከሩን ካሊብሬት /ስልጣን ባለው አካል ልኬት ለማወቅ/ በተደጋጋሚ በሀገር ውስጥ ካሊብሬት እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም፤ያልተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

በአገር ውስጥ ሥልጣን ባለው አካል ካሊብሬት ሊደረጉ ያልቻሉ የኤታኖል ታንከሮችን የሚያሳይ ፎቶግራፍ፡፡

99. እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ የ 2006 በጀት ዓመት የኦዲት ዳይሬክቶሬት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት እንደተመለከተው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በተደረገ የነዳጅ ቆጠራ 3,224.86 ሊትር ፔትሮሊየም እና 8,304.95 ሊትር ዲዝል ከካርድ ባላንስ ጋር ሲነፃፀር በማነስ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ከላይ ለተከሰቱት ችግሮች የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

100.ስለ ሁኔታው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የቢሮ አገልግሎትና ቋሚ ንብረት አስተዳደር አስተባባሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በእ.ኤ.አ 2012/2013 እና 2013/2014 በጀት ዓመት በቆጠራ ወቅት ያልተገኙ የሚለው መረጃው ሙሉ ለሙሉ ስህተት ያለው ሲሆን እ.ኤ.አ በ 2014/15 በጀት ዓመት የተስተካከለ ቆጠራ የተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

101.እንዲሁም የኢታኖል ታንከር ካሊብሬት አለመደረግን የነዳጅ ቆጠራን በተመለከተ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በተደጋጋሚ የካሊብሬሽን ጥያቄ በሀገር ውስጥ የቀረበ ቢሆንም ያልተገኘ በመሆኑ የውጭ ሀገር ተቋማትን ማፈላለግ አስፈላጊ በመሆኑ መጠይቅ አቅርበው መልስ በመጠባበቅ ላይ ያሉ መሆኑን ሲገልፁ የነዳጅ ቆጠራን በሚመለከት በመሬት ውስጥ የተቀበረ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከር በሌላ በአዲስ ታንከር በተቀየረበት ወቅት የተከሰተ ችግር መሆኑን ገልፀው ሁኔታውን እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

1. አሮጌው ታንከር ወደ አዲሱ ነዳጅ ታንከር ሲዘዋወር መጨረሻ ላይ ፓንፑ ሊስበው የሚችለው መጠን በውስጥ የቀረ በመሆኑ፣
2. አሮጌውን ታንከር ቀኑን ሙሉ አድርጎ የማዋል አሰራር የነበረ በመሆኑ እና
3. አሮጌው ታንከር ከመሬት ውስጥ ሲወጣ ከታንከሩ ስር ያለው መሬት በነዳጅ የራሰ በመሆኑ እና ታንከሩ መሬት ውስጥ በመቆየቱ ምክንያት ያፈስ የነበረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

102. የቋሚ ንብረት ቆጠራን በተመለከተ የቢሮ አገልግሎትና ቋሚ ንብረት አስተዳደር አስተባባሪ በእ.ኤ.አ 2012/2013 እና 2013/2014 በጀት ዓመት በቆጠራ ወቅት ያልተገኙ የሚለው መረጃው ሙሉ ለሙሉ ስህተት ያለው በመሆኑ እ.ኤ.አ በ 2014/15 በጀት ዓመት የተስተካከለ ቆጠራ የተሰራ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም በ 2014/15 የኦዲት ቡድኑ የተገለፁትን ቋሚ እቃዎች አመሳክሮ ለማግኘት ያልቻለ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበለውም፡፡

103. በስኳር ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ተግባር በዋናው መ/ቤትና በሁሉም ፋብሪካዎች ተመሳሳይ የሆነ የንብረት አመዘጋገብና አያያዝ ስርዓት መዘርጋት ሲሆን፤ከዚህአኳያ ባለመተግበሩ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ወቅት ያልተገኙ ቋሚ ንብረቶች ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ በመሆኑ የአሰራር ክፍተቱ ለምዝበራና ለስርቆት በር እንዲከፈት ምክንያት ይሆናል፡፡

ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ቋሚ ንብረቶች በንብረት አስተዳደር

መመሪያ መሰረት የተወገዱ መሆናቸውን በተመለከተ

104. በእርጅና እና በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የነበር ስኳር ፋብሪካዎች ቋሚ ንብረቶች በኮርፖሬሽኑ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በአስወጋጅ ኮሚቴ ተጣርተው ለውሳኔ ቀርበው እንዲወገዱ ሊደረግ ይገባል፡፡

105. ኮርፖሬሽኑ በእርጅና እና በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የነባር ስኳር ፋብሪካዎች ቋሚ ንብረቶች በኮርፖሬሽኑ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በአስወጋጅ ኮሚቴ ተጣርተው ለውሳኔ ቀርበው እንዲወገዱ ስለመደረጉ ክትትል ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ ከ 2007 በጀት ዓመት የኮርፖሬሽን ኦዲት ዳይሬክቶሬት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በተገኘው መረጃ መሰረት የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በእርጅና እና በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ቋሚ ንብረቶች በአስወጋጅ ኮሚቴ ተጣርተው ለውሳኔ ቀርበው እንዲወገዱ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ እነርሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በንብረት አስተዳደር አወጋገድ መመሪያ መሰረት ባለበት የሚሸጥ 98 እቃዎች
- በመቅበር/ማቃጠል የሚወገድ 19፣
- በእስክራፕ መልክ የሚሸጥ 47
- የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎች 91፣
- የሞተር ቢስክሌቶች 28፣
- ብስክሌቶች 38፣
- ጎማዎች 3943፣
- የመኪና ባትሪዎች 735፣
- የሞተር ቢስክሌት ጎማዎች 1922፣
- የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ቸርኬ 206፣
- ቀላል ጋሪዎች 22፣
- ዲዝል ጀነሬተሮች 4
- በድምሩ 7,153 እቃዎች በኮርፖሬሽኑ የንብረት አስተዳደር መመሪያ አንቀጽ 26 መሰረት ያልተወገዱ መሆኖቸው ታውቋል፡፡

106. በተጨማሪም ከውጭ ሀገር በመርከብ M.V Segalle D and M.V Serra ተጭኖ ከመጣ ስኳር ውስጥ በቁጥር 3,777/ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ሰባት/ ኩንታል ስኳር የተበላሸ በመሆኑ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ግቢ በመቅበር የድርጅቱ የማኔጅመንት አባላትን እና ሌሎች የመስተዳድር አካላትን በቁጥር 13 የሆኑ የስም ዝርዝራቸው የተመለከተ በወሰኑት ውሳኔ የተወገደ መሆኑን በሚያዚያ 13/2007 ዓ.ም ለማስወገድ በማኔጅመንት ከተያዘ ቃለ-ጉባኤ መመልከት ተችሏል፡፡

107. ስለሁኔታው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የቢሮ አገልግሎትና ቋሚ ንብረት አስተዳደር አስተባባሪና የግዥ ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የንብረት አስተዳደር አስተባባሪው ንብረቶችን ለማስወገድ በተለያዩ ጊዜያት የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የተቋቋመ ቢሆንም የኮሚቴው ዓባላት በተለያዩ ምክንያቶች ከድርጅቱ የለቀቁ በመሆኑ የንብረት ማስወገዱ ሂደት እረጅም ጊዜ ለወስድ የቻለ ሲሆን፤ ሆኖም በአሁኑ ወቅት ያለው ኮሚቴ በተቀመጠው የንብረት አወጋገድ ስርዓት መሰረት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ የሚገኝ በመሆኑ በቀጣይነት የማስወገድ ሂደቱን የሚከውን መሆኑን ገልፀዋል፤፤

108. እንዲሁም ከውጭ ሀገር በሁለት መርከቦች ተጭኖ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ በመበላሸቱ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውስጥ በመቅበር ስለመወገዱ የኦዲት ቡድኑ ለግዥ ቡድን መሪ ባቀረበው ቃለ-መጠይቅ ለምን አገልግሎት እንደመጣ፣ በምንስ ምክንያት ሊበላሽ እንደቻለ፤ እንዲሁም በብልሽቱ ምክንያት ከሻጭ ካምፓኒ ካሳ የተጠየቀ ስለመሆኑ ለሚለው በተሰጠ መልስ ከውጭ ተገዝቶ የሚመጣ ስኳር በኮርፖሬሽን ግብይት ዘርፍ በኩል በመሆኑ ምላሹም የሚሰጠው በኮርፖሬሽኑ በኩል ነው በሚል የተገለፀ መሆኑ ታውቋል፡፡

109. በስኳር ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ተግባር የማያገለግሉ ንብረቶችን ለማስወገድ በወቅቱ በ 6 ወር ጊዜ ውስጥ የማስወገድ እርምጃ ሥራ ላይ ማዋል እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም ይህ ባለመፈፀሙ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ከላይ የተዘረዘሩት ለሌላ ድርጅት ቢሸጡ ገንዘብ ማስገኘት እየቻሉ ባለመሸጣቸው ድርጅቱ ገቢ እንዲጣ ሆኗል፡፤

110. በተጨማሪም በሁለት መርከብ መጥቶ ትክክለኛ ማስረጃ ባልተገኘለት መንገድ በመቅበር ተወገደ የተባለው ስኳር ብዛቱ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ አንፃር ካሳ ያልተጠየቀበት በመሆኑ ወደ ብር ቢለወጥ እጅግ ከፍተኛ ኪሳራ እንዲደርስ አድርጓል፡፡

ምርምርና ስልጠና የተሻሻለ የሸንኮራ አገዳ እና ስኳር አመራረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

111.ምርምርና ስልጠና የተሻሻለ የሸንኮራ አገዳ እና ስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ በማውጣት የፋብሪካዎችን ተወዳዳሪነት እንዲጎለብት ሊያደርግ ይገባል፡፡

112.በኮርፖሬሽኑ የምርምርና ስልጠና ዘርፍ የተሻሻለ የሸንኮራ አገዳ እና ስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ በማውጣት የፋብሪካዎች ተወዳዳሪነት እንዲጎለብት ክትትል ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የሸንኮራ አገዳ ማሳዎችን ምርታማነት ለማሻሻል ኦፕሬሽን ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ በስኳር ፋብሪካው ባለሙያዎች የተሰጡ አስተያቶች ተካቶ ከነመከታተያ ሰነዱ እንዲደርስ የተደረገ መሆኑ፣

113.እንዲሁም ምርታማነትን የሚያሳድጉና የማምረቻ ወጪን የሚቀንሱ የምርምር ቴክኖሎጂዎች በስርፀት/ስልጠና/ መድረክ የተላለፉ ሲሆን፣በስፋት እንዲተገበሩ በቴክኒክ ኮሚቴ በኩል እንዲገመገሙ አቅጣጫ የተሰጠ ሲሆን በሰው ሃይል በኩል የማብቃት ሥራ 70 ከመቶ ተግባርና 30 በመቶ የቲዮሪ ስልጠና እየተሰጠ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

114.በተጨማሪም የመሬት ምርታማነትን ለመጨመር የተሰሩ ሥራዎችን በተመለከተ፡-

- ቡከር ቴት በተባለ የውጭ አማካሪ የተጠናው የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ አፈር መለየት ጥናት በተጠየቀው መሰረት የአፈር ለምነትን ክፍፍል የአዋጭነት ጥናት በመሥራት የማዳበሪያ አጠቃቀም እንዲሻሻል መደረጉ፣
- የአፈር ለምነትን በማሻሻል የአገዳ ምርታማነትን በመጨመር የማዳበሪ ወጪን መቀነስ የሚያስችል ከኢታኖል ተረፈ ምርት የሚዘጋጅ የቪናስ ግግር ማዳበሪያ እና የዩሪያ ማዳበሪያ ድብልቅ ሥራ ላይ በማዋል ውጤታማ በመሆኑ ብር 5,335/100 ኪ.ግ/በሄክታር ገቢ የሚያስገኝና የማዳበሪያ ወጪን ብር 1000 በሄክታር የሚያስቀር በስርፀት/ስልጠና በኩል እንዲተዋወቅ የተደረገ መሆኑ ተገልጿል፡፡

115.በቲሹ ከልቸር ብዜት ከፍተኛ የስኳር ይዘት ያላቸው ቶሎ የሚደርሱና በሽታና ተባይ የሚቋቋሙ የኩባ ሸንኮራ አገዳ ዝርያዎች እንዲተዋወቁ የተደረገ ሲሆን፣ በመተሐራ በቀድሞው አሰራር ከአንድ ሄክታር የዘር አገዳ 10 ሄክታር ይሸፈን የነበረውን በቲሹ ከልቸር ብዜት ዘዴ በተዘጋጀ አንድ ሄክታር ዘር 20.3 ሄክታር መሸፈን የተቻለ ሲሆን፣ ይህ ቴክኖሎጂ ከ 30- 40 ሄክታር እንደሚሸፍን በጥናት ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የቲሹከልቸር ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተባይና በበሽታ የሚጠቁ ዝርያዎችን የመከላከል አቅማቸው እንዲሻሻል በማድረግ ለተባይና ለበሽታ ቁጥጥር ይወጣ የነበረውን ወጪ ከ 25- 30 በመቶ ማምረቻ ወጪ እንዲቀንስ ያደረገ ቴክኖሎጂ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ በምርምር የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች ገንዘብና ሀብት የወጣባቸው

በመሆናቸው በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከማድረግ አንፃር የተጠያቂነት ስርዓት በመዘርጋት ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

116.ስለሁኔታው በስኳር ኮርፖሬሽን የመተሐራ ምርምር ጣቢያ ቡድን መሪ በሰጡት መልስ አሁን ባለው የምርምር ፋሲሊቲና አቅም የሸንኮራ አገዳ ዝርያዎችን ከውጭ ሀገር በማስገባት የማላመድ ሥራ በመሥራት በአጭር ጊዜ በ 12 ወራት ተቆርጠው ለፋብሪካ የሚደርሱ ከፍተኛ የስኳር ይዘት ያላቸውና በሽታና ተባይ የመቋቋም አቅም ያላቸውን 10 ዝርያዎች በ 2007 ዓ.ም በስፋት በመተሐራና በወንጂ ወደ ምርታማነት ሂደት እንዲገቡ የተደረገ መሆኑን፣ እንዲሁም ከፈረንሳይ፣ ከኩባ፣ ከህንድ፣ ከአውስትራሊያ እና ከሱዳን የገቡ ከ130 በላይ ዝርያዎች በመተሐራ መነሻ ዝርያቸውን በማባዛት በተለያዩ ፕሮጀክቶች የማላመድ ሥራ እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

117.የቲሹ ካልቸር ቴክኖሎጂን በተመለከተ በስኳር ኮርፖሬሽን እና በመቀሌ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ለአራት ዓመታት 160 ሚሊዮን ችግኝ በብር 3 ሂሳብ በብር 480 ሚሊዮን በተፈረመ ውል እስከ የኦዲቱ ቃለ-መጠይቅ እስከ ቀረበበት 16/10/2008 ድረስ 7100000/ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ.ህ/ ችግኝ ቀርቦ በማባዛት በአጠቃላይ 193.8 ሄክታር በላይ መሬት በቲሹ ካልቸር መነሻ አገዳ ተሸፍኖ የሚገኝ መሆኑን ገልፀው አሁን ባለው ሁኔታ ከበፊቱ የተሻለ የምርምር ቴክኖሎጂ መጠቀም ፍላጎት ቢኖርም ፋብሪካዎች ከልማዳዊ አሰራር ተላቀው ሳይንሳዊ አሰራርን/የምርምርና ቴክኖሎጂን/ የአሰራር መመሪያ አድርገው ተቀብለው ትርጉም ባለው መልኩ እስካልተቀበሉ ድረስ በሚፈለገው ደረጃ ምርታማነትን ማሻሻል አስቸጋሪ የሚደርገው በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የምርምር ቴክኖሎጂዎችን በስፋት በመጠቀም ውጤት በሚያመጣ መልኩ እንዲተገብሩ የተጠያቂነት አሰራር ሊዘረጋ የሚገባ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

118.በስኳር ኮርፖሬሽን የምርምርና ስልጠና ዘርፍ ሀብትን በመጠቀም ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን በአስደናቂ ሁኔታ ለምርታማነት መሻሻል እያቀረበ ስለመሆኑ በመስክ እይታ በኦዲት ቡድኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ልፋቱ በልማዳዊ አሰራር የሚገታ ከሆነ ወደሚጠበቀው የምርት ማሻሻል ሂደት የማይደረስ ከመሆኑም በላይ የስኳር ምርት ውድድሩን እንዳይሳካ ያደርጋል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ ሀሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በስኳር ኮርፖሬሽን የነባር ስኳር ፋብሪካዎች

የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለተ በስኳር ኮርፖሬሽን እና በናሙና በኦዲቱ ተመርጦ በታየው በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ የታዩ ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሀሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

119.የጨረታ ሂደት እና ድርድር የተከናወነባቸውን ማስረጃዎችን በተደራጀ ሁኔታ ይዞ በሚፈለጉበት ወቅት ማቅረብ አለመቻል የተሰራውን ሥራ ተዓማኒነት የሚያሳጣው መሆኑ፣

120.ኮርፖሬሽኑ የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ያልተከታተለ በመሆኑ በታቀደላቸው ጊዜና በጀት ባለመጠናቀቃቸው ሀገሪቷ ለሌላ ልማት ልታውለው የምትችለው ሀብት ለተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ እንዲውል መሆኑ፣

121. ኮርፖሬሽኑ በስሩ የሚገኙ ፋብሪካዎች በጥራት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የስኳር ምርትና ተጓዳኝ ምርቶች ማምረት እና ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊትር ኢታኖል እንዲመረት ከማድረግ አኳያ ለስኳር ፋብሪካውና ለኢታኖል ፕላንቱ የመለዋወጫ ድጋፍ ባለመደረጉ በእንፋሎት ሃይል እጥረት ምክንያት ኢታኖል ፕላንቱ ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊትር ኢታኖል የማምረት አቅሙን ያልተወጣ መሆኑ፣

122.የስኳር ኮርፖሬሽኑ ከተሰጠው ቁልፍ ተግባር በቂ የቴክኒካል ድጋፍን ክትትል በማድረግ በመስጠት የፋብሪካዎችን ምርታማነት ማሳደግ፣የወጪ ቅነሳ እስትራቴጂ እንዲተገብሩ መደገፍና መከታተልና መቆጣጠር የሚል ቢሆንም የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በምርት ሂደቱ የሚያስፈልጉት መለዋወጫወች በተፈለገው ሁኔታ ባለማግኘቱ ከ 2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት የምርት ዘመን የመለዋወጫ ችግሮች የገጠሙት በመሆኑ ለኢታኖል ፕላንቱ/ፋብሪካ/ ማምረት ሂደት የሚያስፈልግ የእንፋሎት ሃይል ማቅረብ ባለመቻሉ ከምርት ሊያገኝ የሚችለውን ብር 68,661,816.99 እንዲያጣ የተደረገ ሲሆን፣ በግብዓትነት ሊውል የሚችል ሞላስስም ብር 39,193,770 የባከነ መሆኑ፣

123.እንዲሁም ለኢታኖል ፕላንቱ/ፋብሪካ/ ማምረት ሂደት የሚያስፈልግ የእንፋሎት ሃይል ማቅረብ ባለመቻሉ ሀገሪቷ ለተሽከርካሪዎች ነዳጅነት ከ 5-10% በመቀላቀል የምትጠቀምበትን 412,139.8 ሊትር በማምረት ብር 3,915,328.10 እና ለተለያዩ መጠጥ ኢንደስትሪዎች በግብዓትነት የሚሸጠውን ረክቲፋይድ ስፐሪት አልኮሆል 176,631.4 ሊትር በማምረት ብር 2,559,388.99 በድምሩ ብር 6,474,717.09 ያጣች መሆኑ፣

124.በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር የማሽነሪ፣ የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ መስጠት፤ሀብትን አዛውሮ መጠቀም፣ ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ ግብዓቶችን በወቅቱ እንዲቀርቡ ማድረግ ከሚለው አንፃር የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የመለዋወጫ አቅርቦት ባለማግኘቱ ለተደጋጋሚ ጊዜ የቦይለር/የእንፋሎት ሃይል ማመንጫ ክፍሉ/ ለብልሽት በመጋለጡ ምክንያት በተሟላ አቅሙ ባለመሥራቱ በየዓመቱ ከእቅድ በታች ስኳር አምራች ሆኖ በኢታኖል ፕላንቱ/ፋብሪካው/ ላይ ተፅዕኖ በማሳደሩ ኢታኖል አልኮሆል በተሟሉ አቅሙ እንዳያመርት በማድረግ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚያበረክተው አስተዋፆ ያነሰ መሆኑ፣

125.በስኳር ኮርፖሬሽን ግዥና ንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ተግባር ምንም ዓይነት ተገቢ የሆነ ቅሬታ የማይቀርብበት የጨረታ ሂደት ማከናወን እና በውሉ በተመለከተው ጊዜ ግዥ ማጠናቀቅ፤እንዲሁም በስኳር ኮርፖሬሽኑ ግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሐምሌ 2003 አንቀጽ 28.2 መሰረት በኮርፖሬሽኑና በአቅራቢው መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም ከሚለው አንፃር ተግባራዊ ባለመደረጉ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በተፈፀሙ ግዝዎች ያልተገባ ተጨማሪ ወጪዎች እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም በውል ያልታሰረ ግዥም እንዲፈፅም የተደረገ መሆኑ፣

126.በስኳር ኮርፖሬሽን የፋይናንስ ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር ሁሉንም የመንግስት ግዴታዎች መከፈል ካለበት ቀን በ 10 ቀን ቀድሞ በትክክልና ያለምንም ቅጣት መክፈል ከሚለው አኳያ ያልተተገበረ በመሆኑ ኮንቴይነሮች በሞጆ ደረቅ ወደብ ከተወሰነላቸው ጊዜ ገደብ የቆይታ ጊዜያቸው መራዘም ያልተገባ ወጪ/ዲመሬጅ/ እንዲከፍሉ የተደረጉ መሆኑ፣

127.በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ ከተሰጠው ኃላፊነት ከምርት እቅድ ጋር የተጣጣመ የግብዓት አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ በግብዓት ምክንያት የሚፈጠርን የሥራ መቆምን ወደ ዜሮ ማድረስ ከሚለው አንፃር ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ባለመተግበሩ ለመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶባቸው የመጡ መለዋወጫዎች በትዕዛዝ መሰረት ባለመቅረባቸው በስኳር ፋብሪካው የስኳር እና በኢታኖል ፕላንት ኢታኖል አልኮሆል ማምረት ሂደት ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ዓመታዊ የምርት እቅዳቸው ግቡን እንዳይመታ ከመደረጉም በላይ ክሌም የተጠየቀባቸውም መለዋወጫዎች ወቅታዊ ክትትል ያልተደረገባቸው በመሆኑ ከፍተኛ ገንዘብ እንዳይመለስ መደረጉ፣

128.በስኳር ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ተግባር በዋናው መ/ቤትና በሁሉም ፋብሪካዎች ተመሳሳይ የሆነ የንብረት አመዘጋገብና አያያዝ ስርዓት መዘርጋት ሲሆን፣ ከዚህ አኳያ ባለመተግበሩ በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ወቅት ያልተገኙ ቋሚ ንብረቶች ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

129.በስኳር ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ተግባር የማያገለግሉ ንብረቶችን ለማስወገድ በወቅቱ በ 6 ወር ጊዜ ውስጥ የማስወገድ እርምጃ ሥራ ላይ ማዋል እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ያልተወገዱ መሆኑ፣

130.በተጨማሪም 3777/ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰበሰባት/ ኩንታል ስኳር በሁለት መርከብ መጥቶ ትክክለኛ ማስረጃ ባልተገኘለት መንገድ በመቅበር የተወገደ መሆኑ፣

131.በስኳር ኮርፖሬሽን የምርምርና ስልጠና ዘርፍ ሀብትን በመጠቀም ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን በአስደናቂ ሁኔታ ለምርታማነት መሻሻል እያቀረበ ስለመሆኑ በመስክ እይታ በኦዲት ቡድኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በልማዳዊ አሰራር እንዳይገታ የተጠያቂነት አሰራር ስርዓት ሊዘረጋለት የሚገባ መሆኑ፣

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

132.ኮርፖሬሽኑ የጨረታ ሂደት እና ድርድር የተከናወነባቸውን ማስረጃዎችን በተደራጀ ሁኔታ ሊይዝ/እንዲያዝ ሊያደርግ ይገባል፡፡

133.ኮርፖሬሽኑ የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በታቀደላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ሊያደርግ ይገባል፡፡

134.ኮርፖሬሽኑ በስሩ የሚገኙ ፋብሪካዎች በጥራት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የስኳር ምርትና ተጓዳኝ ምርቶች እንዲያመርቱ እና ከ 1 ቶን ሞላስስ 280 ሊትር ኢታኖል እንዲመረት የመለዋወጫ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

135.ኮርፖሬሽኑ በቂ የቴክኒካል ድጋፍን በመስጠት እና ክትትል በማድረግ የፋብሪካዎችን ምርታማነት ሊያሳድግ፣የወጪ ቅነሳ እስትራተጂ እንዲተገበር ድጋፍ ሊሰጥ፣ ሊከታተልና ሊቆጣጠር፤እንዲሁምለስኳር ፋብሪካ እና ለኢታኖል ፕላንት በምርት ሂደቱ የሚያስፈልጉት መለዋወጫወች በተፈለገው ሁኔታ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

136.ኮርፖሬሽኑ ለስኳር ፋብሪካዎች እና ለኢታኖል ፕላንት የማሽነሪ፣ የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ መስጠት፤ሀብትን አዛውሮ መጠቀም፣ ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ መለዋወጫዎችን እና ግብዓቶችን በወቅቱ እንዲቀርቡ ማድረግ አለበት፡፡

137.ኮርፖሬሽኑ ባወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ቅሬታ የማይቀርብበት የጨረታ ሂደት በማከናወን በአቅራቢው እና በግዥ ፈፃሚ መካካል ውል መፈረሙን ሊከታተልና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

138.ኮርፖሬሽኑ የመንግስት ግዴታዎችን መክፈል ካለበት ቀን በ 10 ቀን ቀድሞ በትክክልና ያለምንም ቅጣት ሊከፍል ይገባል፡፡

139. ኮርፖሬሽኑ መለዋወጫዎች በትዕዛዝ መሰረት መቅረባቸውን ሊቆጣጠር እና ክሌም የተጠየቀባቸው መለዋወጫዎች ወቅታዊ ክትትል እንዲደረግባቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡

140.ኮርፖሬሽኑ በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ወቅት ለሚታዩ ቋሚ ንብረቶች ጉድለት ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ/እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

141. ኮርፖሬሽኑ በእርጅና እና በተለያዩ ምክንያቶች በስኳር ፋብሪካ መጋዘኖች የሚገኙ ቋሚ ንብረቶችን ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ሊያስወግድ ይገባል፡፡

142.በስኳር ኮርፖሬሽን የምርምርና ስልጠና ዘርፍ እየተካሄደ ያለው ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ለምርታማነት መሻሻል የማቅረብ ሂደት በልማዳዊ አሰራር እንዳይገታ የተጠያቂነት አሰራር ስርዓት ሊዘረጋለት ይገባል፡፡